ቀን /Date መስከረም 2 0 2012

ቁጥር/Ref. ሚ/ሳ/ኮ/ሚኒ/ር/ደ/ክ/ዘ/ጽ/ከ

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ለአ/አበባ ሳይ/ቴክ/ ዩኒቨርሲቲ
ለአዳማ ሳይ/ቴክ/ ዩኒቨርሲቲ
ለሐረማያ ዩኒቨርሲቲ
ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ
ለባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ
ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ
ለሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ
ለዲላ ዩኒቨርሲቲ
ለጅማ ዩኒቨርሲቲ
ለመቐለ ዩኒቨርሲቲ
ለአክሱም ዩኒቨርሲቲ
ለደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ
ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
ለደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ
ለድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ
ለጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ
ለመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ
ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
ለሠመራ ዩኒቨርሲቲ
ለወሎ ዩኒቨርሲቲ
ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ
ለወለጋ ዩኒቨርሲቲ
ለአምቦ ዩኒቨርሲቲ
ለቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ
ለአሶሳ ዩኒቨርሲቲ
ለወልዲያ ዩኒቨርሲቲ
ለአዲግራት ዩኒቨርሲቲ
ለወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ
ለዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ
ለመቱ ዩኒቨርሲቲ
ለጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ
ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ
ለሰላሌ ዩኒቨርሲቲ
ለኦዳቡልቱም ዩኒቨርሲቲ
ለራያ ዩኒቨርሲቲ
ለእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ
ደባርቅ ዩኒቨርሲቲ
ለመቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ
ለቦንጋ ዩኒቨርሲቲ
ለወራቤ ዩኒቨርሲቲ
ለጂንካ ዩኒቨርሲቲ
ለደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ
ለቀብሪደሃር ዩኒቨርሲቲ
ለኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ

ጉዳዩ፡- **የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ዲስፕሊን መመሪያን ስለመላክ፣**

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የዲስፕሊን መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

በዚህ መመሪያ ውስጥ በተገለጹ ጉዳዮች ላይ አከራካሪ ወይም ማብራሪያ የሚፈልጉ ነጥቦች ሲያጋጥሙ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በኩል ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴርን መጠየቅ የሚቻል ሲሆን ዩኒቨርሲቲዎች የዚህን መመሪያ ይዘትና ትርጉም ሳይቀንሱና ሳይቀይሩ በተጨማሪነት እንደየራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ሊካተቱ የሚገባቸውን ጉዳዮችን የመመሪያው አካል ማድረግ ይችላሉ፡፡

ስለሆነም መመሪያው በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ለነባርና አዲስ ተማሪዎች በቂ ግንዛቤ በመፍጠርና ተደራሽ በማድረግ እንዲሁም ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በማሳወቅ ለውጤታማነቱም የቅርብ ክትትል እየተደረገ እንዲተገበር አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ፕሮፌሰር ወ/ማርያም ተከተል (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

- ለሚኒስትር ፅ/ቤት
- ለሚኒስትር ዴኤታ ፅ/ቤት (3)

ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የዲስፕሊን መመሪያ

(መመሪያ ቁጥር፡ ሳከትሚ/002/2012)

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
መስከረም 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

መግቢያ

ትምህርት ለሀገር ብልፅግና ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡ በዚህም ባለፉት ሶስት የኢንዱስትሪ አብዮቶች የሰው ልጆችን ኑሮ በማዘመንና በማቅለል ዓለም ወደ ደረሰበት ደረጃ ያሸጋገረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ዓለማችን ሰው ሰራሽ ብልህነትንና ናኖ ቴክኖሎጂን እየተገበረች ባለችበት በአራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ላይም የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ዓለም የደረሰበትን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥበብ በመጠቀም የህብረተሰብን ኑሮ ማሻሻል እንዲቻል በዕውቀትና በክህሎት የበለጸገ ዜጋ ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጆች ክብርና እና ብልጽግና ቅድሚያ የሚሰጥ በመልካም ስነ ምግባር የዳበረ ትውልድ ለማፍራት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያደርጉትን ጥረት መደገፍ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው እናት ሀገራቸውና ቤተሰቦቻቸው የጣሉባቸውን ኃላፊነት በመገንዘብ ዝርዝር መብትና ግዴታቸውን አውቀው የግልና የጋራ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ለሌሎች ወጣቶች መልካም አርዓያ እንዲሆኑ ለማስቻል፤

ለተማሪዎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመተሳሰብ፣ የመከባበር፣ የመቻቻልና በጋራ የመኖር ጥበብ ሥልጠና ማዕከል እንዲሆኑ ለማስቻል፤

በተማሪዎች ላይ የስነ ልቦናም ይሁን አካላዊ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ለመከላከል እንዲሁም ህጋዊና ፍትኃዊ የዲስፕሊን ጥሰት እርምጃ አወሳሰድ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው የተቋሙን ህግ፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ እሴቶች እና የሌሎችን ሰብኣዊና ዴሞክረሲያዊ መብቶችን እንዲያውቁ፣ እንዲያከብሩ እና እንዲያስከብሩ ለማስቻል

ሰላማዊ የመማር ማስተማርን ሂደትን ለማረጋገጥና ለማስቀጠል እንዲሁም መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እንዲያግዝ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ወጥ የሆነ መመሪያና አተገባበር እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፤

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ይህንን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የዲስፕሊን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1፡ አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የዲስፕሊን መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አንቀጽ 2፡- ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ መሰረት፡-

1. "ዩኒቨርሲቲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የተቋቋመ የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡
2. "ሴኔት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 49 መሠረት የተቋቋመና በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አካደሚክ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሰጭ አካል ነው፡፡
3. "የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 53 መሠረት ዩኒቨርሲቲውን በበላይነት እንዲመራ የተሾመ ነው፡፡
4. "አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተሾመና የዩኒቨርሲቲውን አካዳሚያዊ ጉዳዮች የሚመራ ነው፡፡
5. "የአስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተሾመና የዩኒቨርሲቲውን አስተዳደራዊ ጉዳዮች የሚመራ ነው፡፡
6. "የተማሪዎች ህብረት ፕሬዚዳንት" ማለት የዩኒቨርሲቲውን ተማሪዎች ሕብረት እንዲመራ በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች የተመረጠ ተማሪ ነው፡፡
7. "የተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር" ማለት በግቢው ለሚገኙ ተማሪዎች መሠረታዊ አገልግሎቶችን የሚሰጥ፣ የሚያስተባብርና የሚያስተዳድር አካል ነው፡፡
8. "ተማሪ" ማለት በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት መርሃ ግብሮች ተመዝግቦ በመማር ወይም አጭር ስልጠና በመውሰድ ላይ ያለ ነው፡፡
9. "ዕጩ ተመራቂ" ማለት ለመመረቅ የሚያስችሉ ሁሉንም ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ የምረቃ ስነ-ስርዓት እስኪከናወንና የትምህርት ማስረጃ ተሰጥቶት እስኪወጣ ያለ ነው፡፡
10. "የተማሪዎች የዲሲፕሊን ኮሚቴ" ማለት በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት የሚቋቋም ሆኖ በዲሲፕሊን ጥፋት የሚከሰስን ተማሪ ጉዳይን በዚህ የዲስፕሊን መመሪያ መሠረት እየመረመረ ጥፋቱን የሚመጥን የውሳኔ ሃሳብ ለአስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት የሚያቀርብ አካል ነው፡፡
11. "አዋጅ" ማለት የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴርን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 1097/2011 እና የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 ማለት ነው፡፡
12. "የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማህበረሰብ" ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 28ና 34 ከተገለጸው በተጨማሪ ተማሪዎችን እንዲሁም በግቢ ውስጥ የሚገኝን ከተቋሙ ጋር ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው ይጨምራል፡፡
13. "ስነ ምግባር' ማለት ማንኛውም በተቋሙ ወይም በተቋሙ ማህበረሰብ አባላት ወይም ከተቋሙ ውጭ ባለ ማህበረሰብ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳርፍ የሚችል ባህሪይ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ሊገለጽ የሚችል ነው፡፡
14. "የተማሪዎች ህብረት" ማለት በዩኒቨርሲቲው ወይም በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ወይም በሀገር አቀፍ የተማሪዎች ህብረት በሚወጣ ህግ መሠረት የተቋቋመ በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ተመርጦ የተማሪን ውክልና የያዘ አካል ነው፡፡

15. "የተማሪዎች ክበብ" ማለት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው የግል ችሎታቸውን ለሌሎች በማካፈልና ከሌሎችም ለመማር፣ የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ ለማገዝና ለማስተማር፣ እንዲሁም ችግሮችን በጋራ ለመፍታት በተማሪዎች ፍላጎት የተቋቋመ የተጓዳኝ ትምህርት አካል ሆኖ በዩኒቨርሲቲው ዕውቅና ያገኘ ማለት ነው።
16. "ማህበራዊ አገልግሎት" ማለት ተማሪው በጥፋቱ የተነሳ የሚወሰንበት ቅጣት ሆኖ ተማሪው ያለ ክፍያ በተመደበበት በታ የሚሠራው የጉልበት ወይም የአዕምሮ ስራ ነው።
17. "የዩኒቨርሲቲው ሀብት" ማለት በዩኒቨርሲቲው ባለቤትነት ወይም በአደራ የተያዙ (የተመዘገቡ) ንብረቶችን ያጠቃልላል።
18. "የዲሲፕሊን ጥፋት" ማለት በዚህ መመሪያ ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጐች የተከለከለ ድርጊት መፈፀም ወይም መተባበር ወይም ሲፈጸም እያዩ በቸልተኝነት ማለፍ ነው።
19. "የዲስፕሊን መመሪያ" ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 1152/2011 አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የወጣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የዲስፕሊን መመሪያ ነው።
20. "አነስተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች" የሚባሉት ለዲስፕሊን ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ በዚህ መመሪያ መሠረት ኃላፊነት በተሰጠው አካል የምክር፣ የቃል ወይም የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው።
21. "ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች" የሚባሉት ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና እንደአስፈላጊነቱ ማህበራዊ አገልግሎት በመስጠት የሚያስቀጡ ዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው።
22. "መካከለኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች" ከአንድ ወሰነ ትምህርት እስከ ሁለት ዓመት የሚያስቀጡ (ከትምህር ገበታ የሚያሳግዱ) የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው።
23. "ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች" የሚባሉት ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጡ (ከትምህርት ገበታ የሚያሳግዱ) የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው።
24. "በጣም ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች" የሚባሉት ከዩኒቨርሲቲው የትምህርት መርሃ-ግብር ሙሉ በሙሉ መሰናበትን የሚያስከትሉ የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው።

አንቀጽ 3፡- የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አግባብ ካላስገደደ በስተቀር በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

አንቀጽ 4፡- የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ባሉ በተለያዩ የትምህርት መርሃ ግብሮችና የቅበላ ዓይነቶች ተመዝግበው ትምህርታቸውን በሚከታተሉ ተማሪዎችና ዕጩ ተመራቂዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት
መብቶችና ግዴታዎች

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 በአንቀጽ 38ና 39 የተዘረዘሩትን እንዳሉ ሆነው በተጨማሪ የተማሪዎች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ክፍል ቀርበዋል።

አንቀጽ 5፡- የተማሪዎች መብቶች፣

1. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሴኔት ባወጣው የትምህርት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በነጻነት የመማር፣ የመጠየቅ፣ የመመራመር፣ የመረዳዳት፣ የማወቅ፣ ሳይንሳዊና ጥበባዊ ክህሎትን የማሳደግ፣ ልቆ መገኘት፣
2. በመማሪያ ክፍል፣ በዩኒቨርሲቲ ግቢና በህብረተሰቡ ውስጥ ለመማር አመቺ ሁኔታን የማግኘትና የመጠቀም፣
3. በዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ ህገ-መንግስታዊና ሰብዓዊ መብታቸውና ደህንነታቸው ተጠብቆ የመኖር፣
4. በዩኒቨርሲቲ ጉዳዮች ላይ በህጋዊና በሰላማዊ አግባብ አቋማቸውን በነጻነት የማራመድ፤
5. ማንኛውንም አይነት አድሎ ወይም ትንኮሳ እንዳይደርስባቸው ህጋዊ ከለላን የማግኘት፤
6. በማንኛውም የመምህርና የተማሪ ግንኙነት የፍትህና ፍትሃዊነት ተጠቃሚ የመሆንና ለመማር የሚያነሳሳ መልካም ተቋማዊ ድባብን የማግኘት፤
7. ስለአካዳሚያዊ ብቃታቸው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ በተደነገጉ መርሆዎችና በዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ መመዘኛዎች መሰረት የመመዘን፣ ኢ-ፍትኃዊ ምዘና ሲፈጸም ቅሬታን በዩኒቨርሲቲው ስርዓት መሠረት በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የማቅረብና ፍትሕን የማግኘት፤
8. ግልጽነት ባለው ስርዓት መሠረት የመምህራንንና ሌሎች አካዳሚክ ሰራተኞችን የስራ አፈጻጸም መመዘንና የአፈጻጸም ግምገማው ላይ በመሳተፍ አስተያየት የመስጠት፣
9. በትምህርት ማህደራቸው ዉስጥ የሚቀመጡ መረጃዎች በሚስጢር ስለሚጠበቁበትና ለሌላ ወገን ስለሚገለጹበት ሁኔታ የሚወስን አስማማኝ ስርዓት ተጠቃሚ የመሆን፣
10. የተማሪው የጋራ ጥቅሞችን በህጋዊ መንገድ እንዲጠበቁ ለማስቻል አግባብነት ባላቸው ህጎች በተቋቋመና የዩኒቨርሲቲውን ተማሪዎች በሙሉ በአባልነት በሚያቅፈው የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ህብረት አባል የመሆን፣
11. በዩኒቨርሲቲው ደንብና ስርዓት መሠረት በግልም ሆነ በማህበራቸዉ አማካይነት በዩኒቨርሲቲው መገልገያዎች የመጠቀም፤
12. በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ድንጋጌዎችና የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት በማህበራቸው ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት በተለያዩ የዩኒቨርሲቲው አካደምያዊና አስተዳደራዊ ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ፤
13. የፈተና ውጤትን በወቅቱ የማየት፣ ቅሬታ ካለ የማቅረብ
14. የፈተና ውጤት /Grade Report/ በወቅቱ የመቀበልና አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች በማቅረብ አግባብነት ያለው የትምህርት ማስረጃ በጊዜ የማግኘት፣
15. የየሴሚስተሩን የመጨረሻ የፈተና ፕሮግራም በቂ በሆነ ጊዜ (ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት) የማወቅ፣
16. ማንኛውም መደበኛ ተማሪ የወጭ መጋራት ውል ከፈረመ ወይም ለአገልግሎቱ የሚገባውን ክፍያ በቅድሚያ እስከ ፈፀመ ድረስ ዩኒቨርሲቲው የሚሰጠውን የምግብ፣ የመኝታ፣ የህክምናና የመዝናኛ አገልግሎቶችን የማግኘት፣
17. ከትምህርት ጋር አግባብነት ያላቸውን ሀሳቦች የማቅረብ፣ የመከራከርና የመወያየት፣

18. ከዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጋር ለሚፈጠሩ ማንኛውም የዲሲፕሊን ግድፈቶች (አለመግባባቶች) አግባብነት ያለው ፍትህ የማግኘት እና በተገቢው አካል የመዳኘት፣
19. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚቋቋሙ የተማሪዎች ክበባትና ሌሎች አግባብነት ባላቸው አደረጃጀቶች (ለምሳሌ የመኝታ ቤት፣ የመኖሪያ ሕንፃ፣ የዲስኘሊን፣ የመዝናኛ፣ የምግብ ቤት፣ የፀረ-ኤድስ፣ የጤና፣ የአካባቢ፣ የስፖርትና የመዝናኛ ወዘተ) ውስጥ በአመራርነት ሆነ በአባልነት የመሳተፍ፣
20. በዩኒቨርሲቲው የሚሰጡ አገልግሎቶች በእኩልነትና በፍትሃዊነት የማግኘት፣
21. በዩኒቨርሲቲው ህገ ደንብ /Legislation/ የተካተቱትን መብቶች በአግባቡ የመጠቀም፡
22. በጥፋተኝነት በሚከሰሱበት ጊዜ የተከሰሱበትን ወይም የተጠረጠሩበትን ጉዳይ በተመለከተ የበኩላቸውን ማስረጃና ክርክር የማቅረብ፣
23. በአካዳሚክና በአስተዳደራዊ ነክ ጉዳዩች ዙሪያ በሰላማዊ ሁኔታ የመወያየትና ሐሳብ የመስጠት ብሎም ፓናል ውይይት የማዘጋጀት፣
24. በሥራቸውና በችሎታቸው መሰረት ያለ ምንም አድልዎ የመገምገምና የግምገማ ውጤታቸውን የማወቅ፣ ቅሬታ ካላቸውም ስርአትን ተከትሎ የፈተና ወረቀቶቻቸውና የተገመገሙባቸው ስራዎቻቸው እንደገና እንዲታይላቸው የማመልከት፣ ውጤቱንም የማወቅ፣
25. በዩኒቨርሲቲው ህገ ደንብ (Legislation) መሰረት በማንኛውም የመማር ማስተማርና አገልግሎት በሚሰጥበት መስክ በብሄር፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ ወገንተኝነት ምክንያት አድልዎ የማይደረግባቸው መሆኑን መረዳት፤ ከተደረገባቸውም ለሚመለከተው የአመራር አካል ቅሬታቸውን የማቅረብና ምላሽ የማግኘት፤
26. የምግብ አገልግሎት ከዩኒቨርሲቲው የማይፈልጉ ተማሪዎች ማመልከቻ አቅርበው የሚመለከተው አካል ሲፈቅድ በወጪ መጋራት ደንብ መሰረት በወር ለምግብ የተበጀተውን ገንዘብ የመውሰድ መብት
27. ቤተ መጻሕፍቶችና ወርክሾፖች እንዲሁም ሌሎች ትምርታቸውን ሊያግዙ የሚችሉ የዩኒቨርሲቲውን ወይም የሌሎች ተቋማትን በሚመለከትው አካል ክትትል የመጠቀም መብቶች አሏቸው፡፡

አንቀጽ 6፡- የተማሪዎች አጠቃላይ ግዴታዎች፣

1. ትምህርት ይጀመራል በተባለው የጊዜ ገደብ በዩኒቨርሲቲው በአካል ተገኝቶ የመመዝገብና አስፈላጊውን ፎርማሊቲዎች አሟልቶ ትምህር የመጀመር፣ በክፍል የመገኘትና ትምህርቱን በሚገባ የመከታተል፣
2. የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና የዩኒቨርሲቲውን መሪ እሴቶች የማወቅና የማራመድ፤
3. አግባብነት ያላቸውን የሀገሪቱን ህጎች፣ የዩኒቨርሲቲውን የተማሪዎች ዲስፕሊን መመሪያ፣ የተቋሙን የሴኔት ደንብ እንደዚሁም ሌሎች ተፈፃሚነት ያላቸውን ህጎች የማወቅ፣ የማክበርና የማስከበር በነሱም የመመራት
4. ከማንኛውም ማህበረሰብ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ሕገ-መንግስታዊ መብቶቻቸውን የማክበር፤
5. የግልም ሆነ የጋራ የተማሪዎች ጥቅም አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ፍጹም ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ቅሬታን በማሰማት በጋራ መፍትሄ የመሻት፤
6. የዩኒቨርሲቲውን የጋራም ይሁን የግል መገልገያ ንብረት በጥንቃቄ የመያዝና የመጠቀም ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት ምክንያት በዩኒቨርሲቲው ንብረት ላይ ለሚያደርሰው አደጋና ለሚከሰተው ማንኛውም ጉዳት በጋራም ሆነ በግል ተጠያቂ

የመሆን፣ እንደዚሁም የደረሰውን ጉዳት የመተካት፤ ጥፋት ያደረሰውን አካል የማጋለጥ፤

7. ዩኒቨርሲቲው ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች መከፈል የሚገባውን ክፍያ የመፈፀም፤
8. ሁልጊዜ የመገልገያ/የመታወቂያ ካርድ መያዝና ለሌላ አካል አሳልፎ አለመስጠትና በሚመለከተው አካል ሲጠየቁ የማሳየት፣
9. በተመዘገቡበት የትምህርት መስክ የተቀመጡ የብቃት መመዘኛዎችን ማሟላት፣ የላቦራቶሪ ሪፖርቶችን እና ሌሎች በመምራን የተሰጡ ሥራዎችን በወቅቱ አጠናቆ ማሰረከብ፣
10. በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ለእያንዳንዱ የትምህርት ኮርስ (ዓይነት) በሚወጣው ኘሮግራም መሰረት በሌክቸር፣ በላቦራቶሪ፣ በወርክሾኘና በመስክ በመገኘት ትምህርቱ የሚጠይቀውን ተግባራትን የማከናወን፣
11. በዩኒቨርሲቲው የተደነገገውን የምሽት መግቢያና መውጫ ሰዓት ማክበር፤
12. ማንኛውንም መምህር፣ የአስተዳደር ሰራተኛ እንዲሁም የመማር ማስተማርንና የአስተዳደር ሂደቱን የመምራትና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለውን አካል የማክበር፣
13. ሰልፍ ባለበት ቦታ ሁሉ ሰልፍን ጠብቆ መገልገል፣
14. በማንኛውም ጊዜ ግቢውን ሲለቁ የተረከቡትን ንብረት በአግባቡ ቆጥሮ ማስረከብ፣ ክሊራንስ በማውጣት ግቢውን በወቅቱ መልቀቅ፣
15. ሱስ ከሚያስይዙ (ጫት፣ ሲጋራ፣ አልኮል፣ ሺሻና የመሳሰሉት) ጎጂ ልማዶች ራስን መጠበቅ፣
16. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ደንብ መሰረት ለትምህርትና ለአገልግሎት ተገቢውን ክፍያ መክፈል ወይም የወጪ መጋራትን ውል መፈረም፣
17. ከዩኒቨርሲቲው ካምፓስ ውጪ ካለው ማህበረሰብ ጋር በሚኖረው ግንኙነት በመልካም ስነ-ምግባር አርአያ መሆን፣
18. የሌላውን ባህል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ወዘተ ማክበርና መጠበቅ፣
19. ከማንኛውም ሕገ-ወጥና ከስነ-ምግባር ውጭ ከሆኑ ተግባራት የመቆጠብ፣ ለምሳሌ ከስርቆት፣ አላግባብ በመጮህ ሌላውን ከማወክ፤ ለሕገ-ወጥ ተግባር ሌሎችን ከማነሳሳት፤ ሱስ ከሚያስይዙ (ጫት፣ ሲጋራ፣ አልኮል፣ ሺሻና የመሳሰሉት) ጎጂ ልማዶች ... ወ.ዘ.ተ ራስንና ሌሎችን የመጠበቅ፤
20. አንድ ተማሪ በተለያዩ ምክንያቶች መባረሩን ሲያውቅ ሰበብ አስባቡ ፈልጎ ሌላውን ተማሪ ይዞ ለመጥፋት ያልሆኑ ጥያቄዎችን ማንሳት፣ ሌሎችንም ቀስቅሶ ረብሻ ለመፍጠር መሞከር፣ በማንኛውም ምክንያት ከሌሎች ጋር መጣላትና የመሳሰሉትን ችግሮች ስለሚፈጥር እንደዚህ ዓይነት ተማሪዎችን ለሚመለከተው አካል ጥቆማ በመስጠት በጊዜ መፍትሄ እንዲፈለግላቸው የማድረግ፣
21. ማንኛውም ተማሪ ከዶርሚተሪው ውጭ ሄዶ ያለመተኛት፣ ሌላ ተማሪም አስደርቦ አለመገኘት፣ ያለፈቃድ የመኝታ ክፍል አለመቀያየር
22. በመኝታ ቤት ምንም ዓይነት ተቀጣጣይ ነገሮችን ያለመያዝ፣ ምግብ ማብሰልና ካውያ አለመጠቀም እና ምንም አይነት ሰው ሊጎዳ የሚችል መሳሪያ ይዞ አለመገኘት፣
23. በሁለት ተማሪዎች መካከል የሚነሱ ግላዊ ጥሎችን ወደ ብሔርና ሃይማኖት በመለወጥ ግጭት ውስጥ አለመግባት፣
24. የሚሰጡ የትምህርት የተለያዩ ሥራዎችን በራስ ጥረት መሥራት፣ የሌላ ሰው ሥራ የራስ አስመስሎ አለማቅረብ፣ ለሌላ ሰው ሠርቶ መስጠት ወይም ከሌላ ሰው መውሰድ ወይም መኮረጅ የማይቻልና ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን የመረዳት፤

ክፍል ሶስት
የተከለከሉ ተግባራት

አንቀጽ 7፡- ከላይ በአንቀጽ 6 የተጠቀሱ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በአጠቃላይ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የተከለከሉ ተግባራት

1. በማንኛውም ሁኔታ በተቃራኒ ጾታ ላይ በደል ወይም ጾታዊ ትንኮሳ መፈፀም፣
2. በግቢ ውስጥ በቡድን ሆኖ ማንኛውንም ዓይነት ኃይማኖታዊም ይሁን ፓለቲካዊ እንቅስቃሴ ማድረግ፣
3. ሃይማኖትን፣ ብሔርን፣ ባህልንና ቋንቋን የሚያንቋሽሽ ማንኛውንም ንግግር ማድረግ፤ መጻፍ ወይም ድርጊት መፈጸም
4. ፖለቲካዊና ኃይማታዊ መልዕክት ያላቸውን አልባሳት፣ ቅርጻ ቅርጾች፣ ጌጣጌጦች፣ የተለያዩ ቦርሳዎችና ዕቃ መያዣዎችን መጠቀም
5. ወደ ግቢ ውስጥ ማንኛውም ዓይነት አደንዘዥ እፅ ማዛወር፣ ማብቀል/መትከል፣ ይዞ ወይም ተጠቅሞ ወይም አልኮል ጠጥቶ ወይም ሰክሮ መግባት፣
6. የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞችን በምንም ሁኔታ መሳደብ፣ መዝለፍ፣ ማንጓጠጥ፣ ማስፈራራትና መዛት፣ ያልተገባና ፀያፍ ንግግር መናገር፣
7. የሌሎች ተማሪዎችን ማህበራዊ ኑሮ የሚያውኩ ድርጊቶችንና ንግግሮችን መፈፀም፣ መረበሽ፣ ቁማር መጫወት፣
8. በግቢው ውስጥ በግልም ሆነ በቡድን ፀብ ማንሳት ወይም መደባደብ ወይም ከነዚህ መሠል ተግባራ መተባበር
9. ማንኛውንም የስርቆት ተግባር መፈፀም፣
10. አደጋ የሚያደርስ ማንኛውንም ነገር /ለምሳሌ ስለት ያለው መሳሪያ፣ መርዝ/ ይዞ ወደ ግቢ ወይም አግልግሎት መስጫ ቦታዎች መግባት፣
11. በመማሪያ ክፍሎች እና በምግብ ቤት አዳራሾች እንዲሁም በመዝናኛና በክሊኒክ ቦታዎች በምንም መልኩ ያልተገባ ጩኸት፣ ጠብ፣ ግርግር መፍጠር፣ መረበሽ
12. ከመፀዳጃ ቤቶች ውጭ መፀዳዳት፣
13. በማንኛውም አካል የሚለጠፉ ህጋዊ ማስታወቂያዎችን መገንጠል፣ መቅደድና መሰረዝ፣
14. በአገልግሎት ዙሪያ ቅሬታ ሲኖር ሰላማዊ እና ሕጋዊ መንገድን ተከትሎ መጠየቅ እንጂ አመፅ ማንሳት፣ ማስነሳትና መተባበር
15. በማኛውም የዩኒቨርሲቲው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፣
16. ፀጉርን በተመለከተ፡-
    - 16.1. ለወንዶች፡- ከ1.5 ሴሜ ርዝመት ያልበለጠ ሆኖ ምንም ዓይነት ቅርጽ የሌለውና የተለየ ቀለም መቀባት
    - 16.2. ለሴቶች፡- በአግባቡ የተሠራና ያልተንጨባረረ ሆኖ የተለየ ቀለም መቀባት

17. አለባበስን በተመለከተ፡-
    - 17.1. ለወንዶች፡- የተቦጫጨቀ፣ የተቀደደ ገላን የሚያሳይ ልብስ መልበስ፣ ሱሪን ዝቅ በማድረግ የውስጥ ቁምጣ ማሳየት፤ሌላን ሰው ሊረብሽ የሚችል ከፍተኛ ሽታ ያለው ሽቶ፣ ዶዲራንትና ሌሎችም መጠቀም፣ ከፍ ያለ ድምጽ የሚያወጡ ጫማዎችን መጫማት
    - 17.2. ለሴቶች፡- የተቦጫጨቀ፣ የተቀደደ ገላን የሚያሳይ ልብስ መልበስ፣በማድረግ የውስጥ ቁምጣ ማሳየት፣ ከጉልበት በላይ ያጠረ ቀሚስ መልበስ፣ ሌላን ሰው

ሊረብሽ የሚችል ከፍተኛ ሽታ ያለው ሽቶ፣ ዶዲራንትና ሌሎችም ኮስሞትክስ መጠቀም፣ ከፍ ያለ ድምጽ የሚያወጡ ጫማዎችን መጫማት

18.በግቢ ውስጥ ወሲብ መፈጸም ወይም ግቢ ውስጥ መውለድ፣
19.ለሌላ ሰው ሊሰሙ የሚችሉ ድምጾችን በሞባይል መጠቀም
20.ባልተፈቀደ በር ወይም አጥር ዘሎ መግባትና መውጣት፣
21.የወል /የጋራ/ መገልግያዎችን የግል ማድረግ፣
22.በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ በወንጀለኝነት የተፈረጁ ድርጊቶችን መፈፀም፣

አንቀጽ 8፡- በተማሪዎች መኝታ ቤት የተከለከሉ

1. የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ያልሆነ ወይም የተባረረ ተማሪ በመኝታ ቤት ማሳደር፣ ማኖር፣
2. ተደራራቢ አልጋዎችን መገንጠል፣ ፍራሽ መሬት ላይ አውርዶ መተኛት፣
3. የኤሌክትሪክ መስመሮችን ጠልፎ ለሌላ አገልግሎት ማዋል፣
4. በተቃራኒ ጾታ መኝታ ክፍል መግባት፣ ማስገባት፣
5. በህመም ምክንያት ካልተፈቀደ በስተቀር ምግቦችን ወደመኝታ ክፍል ይዞ መግባት፣
6. የመኝታ ቤት ቁልፍ በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ማስቀረጽ፣
7. በአንድ አልጋ ላይ ከአንድ በላይ ሆኖ መቀመጥ፣ መተኛት፣
8. በመስኮት መውጣት ወይም መግባት፣
9. በማንኛውም ጊዜ በመኝታ ክፍል ውስጥና አካባቢ ጫጫታና ረብሻ መፍጠር፣ የሚረብሽ ድምጽ /ሙዚቃ የሞባል መጥሪያ/ ማሰማት፣
10.የሽንትና ሻወር ቤቶች፣ የልብስና እጅ መታጠቢያ ገንዳዎችን፣ ማስረጊያ ቀዳዳዎቹን አላስፈላጊ የሆኑ /ፕላስቲክ፣ ድንጋይ፣ ጸጉር፣ ጨርቅና ሞደስ ወዘተ.../ ነገሮችን በመክተት እንዲዘጉ ማድረግ፣ መብሳትና መቅደድ፣
11.በመኝታ ክፍል ውስጥ አልጋን መጋረድ /ቴንሽን ቦክስ መስራት/፤
12.ባልታወቀ ሁኔታና ሳይፈቀድ በዶርም ውስጥና አካባቢ ስብሰባ ማድረግና ሰፊ ቁጥር ይዞ በቡድን መንቀሳቀስ፣
13.በዶርም ውስጥና አካባቢ በቡድን ሆኖ መጸልይ ወይም መስገድ፣
14.በዶርም ውስጥ ምግብ ማብሰል፣ ሻይና ቡና ማፍላት፣
15.የመኝታና የፅዳት አገልግሎት ሰራተኞችን ማመናጨቅና መገላመጥ፣ መሳደብ፤ መዝለፍ፤ ስም ማጥፋት፤ ማስፈራራት፣
16.ከተመደቡበት ዶርም ውጪ ያለፈቃድ መቀየር፤
17. በሽንት ቤትና ሻወር ቤት ውስጥ ያልተገቡ ፅሑፎችን መጻፍ ወይም መለጠፍ
18. የተመደቡበትን የመኝታ ክፍል ያለ ፈቃድ መቀየር፤ ባልተመደቡበት መኝታ ክፍል ውስጥ ተዳብሎ መተኛት ወይም አዳብሎ ማስተኛት፣
19.በግድግዳዎች፣ መዝጊያዎች፣ መስኮቶችና ቁም ሳጥኖች ላይ ማንኛውም ጽሁፍ መፃፍ፣ ስዕል መሳል/መለጠፍ፣ ሚስማር መትከል /መምታት/፣
20. በመኝታ ቤት ውስጥና አካባቢ ጫት፣ ስጋራ፣ አልኮሆል መጠጦችንና ሌሎች አደንዛዥ እፆችን ይዞ መግባት ወይም ሲጠቀሙ መገኘት፣
21. የመኝታ ክፍልን በር (የራስንም ሆነ የሌሎችን) ያለፈቃድ መክፈት/መስበር፣
22. በእጅና ፊት መታጠቢያ ገንዳዎች እንዲሁም በዶርም ውስጥና ኮሊደር ልብስ ማጠብ፣

አንቀጽ 9፦ በተማሪዎች ምግብ ቤት ፈፅሞ የተከለከሉ

1. የራስ ባልሆነ መመገቢያ ካርድ መመገብና የራስን የመመገቢያ ካርድ ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት፣
2. ወደ ምግብ ቤት የአንገት ፎጣ፣ ኮፍያ፣ ስሊኘር ጫማ፣ የሌሊት ልብስ፣ ፒጃማ፣ እና ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ ልብሶችንና አለባበሶችን ለብሶ መምጣት፣
3. በምግብ አዳራሽ ውስጥና አካባቢ ከሰራተኞች ወይም ከተማሪዎች ጋር ግጭት መፍጠር፣ ሠልፍ መጣስ
4. በምግብ ዙሪያ ጥያቄ/ቅሬታ ሲኖር በተወካይ አለያም በራስ ስርአትን ጠብቆ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ እንጂ ያልተገባ ባህሪ ማሳየት፣ ሁከት መፍጠር ወይም እንዲነሳ ማድረግ፣
5. በምግብ አዳራሽ ውስጥ እጅን መታጠብ፣
6. በህመም ምክንያት መንቀሳቀስ ከማይችሉ ተማሪዎች በስተቀር ከዳቦ ውጭ ምግብ ከተማሪዎች ምግብ ቤት ማውጣት፤
7. ከቀረበው የምግብ ዓይነት ውጭ የሐኪም ትዕዛዝ ካላቀረቡ በስተቀር መጠየቅ፣ መጨቃጨቅ፣ መጣላት

ክፍል አራት
የተማሪዎች የዲስፕሊን ጥፋት

አንቀጽ 10፦የዲስፕሊን ጥፋት

1. ተማሪ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጸመ የሚባለው በተቋሙ፣ በሰራተኞችና በሌሎች ተማሪዎች መደበኛ እንቅስቃሴና ሥራ ላይ ተገቢ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት የሚፈጥር፣ የሌሎች የተቋሙ ማኅበረሰብ አባላትን መብት የሚጋፋ፣ መልካም ግንኙነትን የሚጥስ ወይም ተቋሙን የሚጎዳ ድርጊት ሲፈጽም ነው።
2. ከላይ በተራ ቁጥር 1 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ተማሪ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሟል የሚባለው
   ሀ. በዚህ መመሪያ የተከለከሉ ወይም የዲስፕሊን ጥፋት ተብለው የተመለከቱትን ተግባራት ሲፈጽም
   ለ. በሌሎች ተቋሙ ወይም የተቋሙ አካል ባወጣቸው ደንቦች ወይም መመሪያዎች ጥፋት ተብለው የተጠቀሱትን ተግባራት ሲፈጽም
   ሐ. በሀገሪቱ ሕግ ጥፋት ወይም የወንጀል ድርጊት ተብለው የተመለከቱትንና ከመማር ማስተማር ወይም አገልግሎት አሰጣጥን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ድርጊቶች ሲፈጽም
   መ. ተማሪው ወደ ፊት በሚሰማራበት ሙያ ከባድ ጥፋት ተብለው የሚታወቁ ድርጊቶችን ሲፈጽም ነው።

ክፍል አምስት
የዲስፕሊን ጥፋቶች ምደባና ቅጣት

አንቀጽ 11፦ አነስተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች፣

በዚህ መመሪያ አነስተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች ተብለው የሚመደቡት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አነስተኛ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች ናቸው።

1. በምክር የሚታለፉ የዲስፕሊን ጥፋቶች፣

1.1. የመመገቢያ እቃዎችን በተገቢው ቦታ ያለማስቀመጥ /ያለመመለስ/

1.2. በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድላቸው ካልሆኑ በስተቀር አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ላይ ተራን አለመጠበቅ፤
1.3. ለመጀመሪያ ጊዜ አልኮል ጠጥቶ ሰክሮ ወደ ግቢ መግባት፣
1.4. በዩኒቨርሲቲው የኢንተርኔት አገልግሎት መስጫ ኮምፒዩተሮች ፖርኖግራፊ/የወሲብ ፊልም/ መመልከት፣
1.5. ባልተፈቀደ ቦታ ማናቸውንም ማስታወቂያ መለጠፍ
1.6. ከበዚህ መመሪያ ከተቀመጠው አለባበስ ውጭ መልበስ እንዲሁም የፀጉር አቆራረጥና አሰራር ውጭ መቆረጥና መሰራት፣
1.7. በመኝ ክፍል ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ጽሑፍ እና/ወይም ስዕል መለጠፍ፣
1.8. የመማሪያ ክፍሎች፣ የአዳራሾችና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ወንበሮችና ጠረንጴዛዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ከቦታ ቦታ ማዛወር፣ አውጥቶ ውጪ ሲጠቀሙ መገኘት፣አውጥቶ ደጅ ጥሎ መሄድ፣
1.9. በምግብ ቤት ውስጥ እጅን መታጠብ፣
1.10. ሌሎች መሰል የሥነ-ምግባር ጥፋቶችን መፈጸም፣

2. የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የዲስፕሊን ጥፋቶች

የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች ሆነው በማስታወሻ መዝገብ የሚያዙ እና ተማሪውም ለጥፋቱ የሚፈርምበት ሆኖ ለተማሪዉ በጽሁፍ የሚሰጡ ናቸው።

2.1. ከላይ የተዘረዘሩትን በምክር የሚታለፉና መሰል የዲስፕሊን ጥፋቶችን በድጋሜ ለሁለተኛ ጊዜ ፈጽሞ መገኘት
2.2. በመኝታ ክፍል ውስጥና በኮሪደር፣ በእጅና ፊት መታጠቢያ ቦታዎች በመተላለፊያ መንገድ ላይ ልብስ ማጠብ፣
2.3. ያለ ፍቃድ ለአንድ ቀን ከግቢ ውጭ ወጥቶ ማደር እንዲሁም ለ2 ቀናት የአቴንዳንስ ክትትልና ቁጥጥር ሪፖርት አለማድረግ፣
2.4. በመማሪያ ክፍሎች፣ በአብያተ መጽሀፍት፣ በመኝታ ህንፃዎችና በሌሎች የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ግድግዳዎች እንዲሁም በወንበሮችና ጠረጴዛዎች ላይ ማንኛውንም ጽሑፍ መፃፍ/ስዕል መሣል፣
2.5. ውሃና የኤሌክትሪክ ሃይል ያለአግባብ መጠቀም (ማባከን)፣ ውሃ ከፍቶና መብራት አብርቶ መሄድ፣
2.6. አብረው ከሚኖሩ የመኝታ ቤት ተጋሪዎችና አብረው ከሚማሩ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች ጋር ተግባብቶና ተስማምቶ አለመኖር፣
2.7. ተቋሙ ባወጣው አሰራር መሰረት መታወቂያ ወይም የምግብ ካርድ እንዲያሳይ ተጠይቆ ፈቃደኛ አለመሆን፤
2.8. አትክልቶችንና አበባዎችን መርገጥ ወይም መቁረጥ፤
2.9. ፍራሽ ከአልጋ አውርዶ መገኘት፣
2.10. የታጠበ ልብስን ከልብስ ማስጫ ቦታ ውጭ ማስጣት፤
2.11. በግቢ ውስጥ ከፍተኛ ድምጽ ወይም ጩኸት በራስ ድምጽ ወይም በማንኛቸውም የኤልክትሮኒክስ መሣሪያዎች በማስሙህ የአካባቢን ፀጥታን ማደፍረስ፤ (በጫማም ይሁን በሌላ መንገድ) እና ማስቲካ እያስጮኹ ማኘክ፣
2.12. ወደ ዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ የተደነገገን የሰዓት ገደብ አለማክበር፤
2.13. ሌሎች መሰል የስነ ምግባር ጥሰቶችን መፈጸም፤

አንቀጽ 12፡- ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች፣

ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና እንደአስፈላጊነቱ ማህበራዊ አገልግሎት በመስጠት የሚያስቀጡ ዲስፕሊን ጥፋቶችን ያካትታል፡፡

1. የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ወይም ከ30 ያላነሰ ከ50 ሰዓታት ያልበለጠ ማህበራዊ አገልግሎት (የጉልበት ሥራ) ወይም በሁለቱም ሊያስቀጡ የሚችሉ የዲስፕሊን ጥፋቶችን
   1.1. ከላይ በአንቀጽ 11 በንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩትን የቃል ማስጠንቀቂያ ወይም ነጻ ማህበራዊ አገልግሎት የሚያሰጡ የዲስፕሊን ጥፋቶች መካከል አንዱን የዲስፕሊን ጥፋት ተፈፅሞ በተወሰደው ቅጣት መሻሻል ሳይታይና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የዲስፕሊን ጥፋት ደግሞ መፈጸም፤
   1.2. በተራ ምድብ ወቅት የመኝታ ክፍልን፣ መጸዳጃ ቤትን፣ የመኖሪያ ሕንፃ ኮሪዶርን፣ የመኖሪያ ሕንጻ አካባቢን አለማጽዳት፣ የራስን አልጋ አለማንጠፍና የግል ንጽህናን አለመጠበቅ፣
   1.3. ግለሰቦችን ለተራ ጥል መጋበዝ፣ ማጣላት፣ ነገር መቆስቆስ፣ ማጋጋል፣ ጥል ሲነሳ አለመገላገል፣ ወገን ለይቶ ማበር፣ በነገር ማቆራቆስ፣
   1.4. ከተፈቀደ ቦታ ውጭ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ቆሻሻ መጣል፤
   1.5. በዩኒቨርሲቲው ተገቢ አካል የተሰጠን ሕጋዊ ትእዛዝ አለማክበር፤
   1.6. ለጋራ ጤንነት አደገኛ የሆኑ ድርጊቶችን መፈጸም፤
   1.7. ግድግዳ በሚስማር ወይም በመሰል ነገር መብሳት፤
   1.8. ያለ ግለሰቡ ወይም ዩኒቨርሲቲው ፈቃድ የግለሰብ ወይም የዩኒቨርሲቲ ንብረት መጠቀም፣
   1.9. የሌላ ሰው መታወቂያ ወይም የምግብ ካርድ መጠቀም፣
   1.10. የተማሪዎች አገልግሎት እና የተማሪዎች ህብረት ሳያውቁ በየትኛውም መንገድ ከተማሪዎች ገንዘብ መሰብሰብ፣
   1.11. የተማሪዎችን ትራንስፖርትና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን በማመቻቸት ሽፋን ለግል ጥቅም ሲባል ተማሪዎችን ከፍተኛ ክፊያ መጠየቅ ወይም እንዲጠየቁ መተባበር፣
   1.12. በተቋሙ ግቢ ውስጥ ሲጋራ ማጨስ፤ ሌሎች አደንዛዥ ዕጾችን መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት፤ ሌሎችም አጭሰው ወይም ይዘው አያዩ ዝም ማለት
   1.13. የጋራ መገልገያዎችን አለአግባብ ለግል ጥቅም ማዋል፣
   1.14. በማንኛውም መልኩ በድጋሜ መመገብና ለመመገብ መሞከር፣
   1.15. አጭበርብሮ የገንዘብ ድጋፍ ከዩኒቨርሲቲው ለማግኘት መሞከር፣
   1.16. ምንም ውክልና ሳይኖር የተማሪዎች ህብረት አባል፣ የክበብ ተጠሪ ነኝ ወዘተ በማለት ሰዎች መረጃ እንዲሰጡት መጠየቅ ወይም ፍቃድ ሳይሰጠው ስራ ለመስራት መሞከር ወይም መስራት፣

2. ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና እንደአስፈላጊነቱ ማህበራዊ አገልግሎት በመስጠት የሚያስቀጡ የዲስፕሊን ጥፋቶች
   2.1. ከላይ በአንቀጽ 12 በንኡስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት የዲስፕሊን ጥፋቶች መካከል አንዱን ወይም ተመሳሳይ የዲስፕሊን ጥሰት ፈፅሞ በተወሰደው ቅጣት መሻሻል ሳያሳዩ ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የዲስፕሊን ጥፋት ደግሞ መፈጸም፤
   2.2. በግቢው ውስጥ በተለይም በጋራ መገልገያ አካባቢዎች ማለትም በመኝታ፣ በመመገቢያና በመማሪያ ክፍሎች፣ በቤተ መፃህፍት፣ በወርክሾፖች፣ በቤተሙከራ በክሊኒክና በዲ.ኤስ.ቲቪ. ወዘተ አካባቢ ያልተገባ ጩኸት ማሰማት፣ ሁከትና ግርግር ማንሳት፣

2.3. ለ2 ቀናት ከዩኒቨርስቲ ግቢ ውጭ ወጥቶ ካደረ እንዲሁም ለሶስት የአቴንዳንስ ክትትልና ቁጥጥር ቀናት ሪፖርት ካላደረገ

2.4. በመጠጥ ሀይል ሰክሮ በግቢው ውስጥ ሁከት መፍጠር (የአካባቢ ፀጥታን ማደፍረስ)፣

2.5. በተቃራኒ ፆታ መኝታ ህንፃ ውስጥ ያለ ፈቃድ ገብቶ መገኘት፣

2.6. ፍራሽ ወይም ትራስ ወይም የፍራሽ ልብስ ቀዶ መገኘት፣

2.7. ባልተፈቀደለት መኝታ ቤት ማደር ወይም የመኝታ ቦታን ያለፈቃድ መቀየር

2.8. ያልተፈቀደለት ሰው በመኖሪያ ቦታ እንዲኖር፣ እንዲዳበል ወይም እንዲያድር ማድረግ፤

2.9. ያለፈቃድ የበሰለ ምግብ ከዳቦ ውጭ ከማንኛውም ቦታ ወደ ዶርም ይዞ ገብቶ ሲጠቀሙ መገኘት፣

2.10. ማንኛውንም የዩኒቨርሲቲውን ንብረት በአግባቡ አለመጠቀም፣ ማበላሸት፣

2.11. ህጋዊ ባልሆነ መንገድ በአጥር ዘሎ ወይም ሾልኮ መግባትና መውጣት፣

2.12. የስብሰባ፣ የኮንሰርትና የፍልም ማስታወቂያዎችን ያለ ተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር ጽ/ቤት እውቅናና ፈቃድ መለጠፍ፣

2.13. በመኝታ ክፍል ውስጥ ያልተፈቀዱ የኤሌክትሪክ እቃዎችን መጠቀም፣

2.14. ለዩኒቨርሲቲው መምህራን፣ ሰራተኞችና ሀላፊዎች ሥራው የሚጠይቀውን አስፈላጊውን ትብብር አለማድረግ፣

2.15. በግቢ ውስጥ ሰ.ጋራ ማጨስ፣

2.16. ህጋዊ ያልሆነ ስብሰባ ወይም በተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር ወይም በዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራር ፈቃድ ያላገኘ ትእይንት ማሳየት ወይም ለማሳየት መሞከር፣

2.17. የራስን ሃይማኖት፣ እምነትና የፖለቲካ አመለካከት ሌሎች እንዲቀበሉ ጫና መፍጠር፣ መረበሽ

2.18. በመግቢያ በርና በአገልግሎት መስጫዎች የመታወቂያ (የመገልገያ) ካርድ ሲጠየቅ ለማሣየት ፈቃደኛ አለመሆን፣

2.19. ሃይማኖታዊ በአሉሎችንና ትዕይንቶችን በግቢው ውስጥ ማካሄድ፣ እንዲካሄዱ መቀስቀስ፣ ማነሳሳት፣ መምራት፣

2.20. ፀጉርን በተመለከተ፡-

2.21.1 ለወንዶች፡- ከ1.5 ሴሜ ያልበለጠ ሆኖ ምንም ዓይነት ቅርጽ የሌለውና የተለየ ቀለም መቀባት

2.21.2 ለሴቶች፡- በአግባቡ የተሠራና ያልተንጨባረረ ሆኖ የተለየ ቀለም መቀባት

2.21. አለባበስን በተመለከተ፡-

2.21.1. ለወንዶች፡- የተቦጫጨቀ፣ የተቀደደ ገላን የሚያሳይ ልብስ መልበስ፣ ሱሪን ዝቅ በማድረግ የውስጥ ቁምጣ ማሳየት፤ሌላን ሰው ሊረብሽ የሚችል ከፍተኛ ሽታ ያለው ሽቶ፣ ዶዲራንትና ሌሎችም መጠቀም፣ ከፍ ያለ ድምጽ የሚያወጡ ጫማዎችን መጫማት

2.21.2. ለሴቶች፡- የተቦጫጨቀ፣ የተቀደደ ገላን የሚያሳይ ልብስ መልበስ፣በማድረግ የውስጥ ቁምጣ ማሳየት፣ ከጉልበት በላይ ያጠረ ቀሚስ መልበስ፣ ሌላን ሰው ሊረብሽ የሚችል ከፍተኛ ሽታ ያለው ሽቶ፣ ዶዲራንትና ሌሎችም ኮስሞትክስ መጠቀም፣ ከፍ ያለ ድምጽ የሚያወጡ ጫማዎችን መጫማት

2.22. ሌሎች መሰል የስነ-ምግባር ጥፋቶችን መፈፀም፣

አንቀጽ 13፡- መካከለኛ ዲስፕሊን ጥፋቶች

ከአንድ ወሰነ ትምህርት እስከ ሁለት ዓመት የሚያስቀጡ የዲስፕሊን ጥፋቶች በዚህ ምድብ ይካተታሉ፡፡

1. ለአንድ ወሰነ ትምህርት ከትምህርት ገበታ የሚያሳግዱ የዲስፕሊን ጥሰቶች
   1.1. በአንቀጽ 12 በንኡስ አንቀጽ 2 የተጠቀሱት ወይም ተመሳሳይ የዲስፕሊን ጥፋት በድጋሜ ፈጽሞ መገኘት፣
   1.2. ፈተና መስረቅ ወይም ፈተና መኮረጅ ወይም ማስኮረጅ፣ የሌላ ሰው ሥራን የራስ አስመስሎ ማቅረብ፣
   1.3. ሴትም ሆነ ወንድ ተማሪዎችን በንግግር፣ በጽሁፍ፣ በስልክ፣ ወዘተ ማስፈራራት፣ ማስቸገር፣ ማስጨነቅ፣ መሳደብ
   1.4. የተለጠፉ ህጋዊ ማስታወቂያዎችን መገንጠል፣ መቅደድ፣ መደለዝ ወይም ማበላሸት፣
   1.5. በምንም ይሁን በምንም ሁኔታ ከተማሪ ጋር ጥል መፍጠር፣ ለድብደባ መጋበዝ
   1.6. የዩኒቨርሲቲውን መምህር፣ ሰራተኛ ወይም ሌሎችን መዝለፍ፣ ማንጓጠጥ፣ መሳደብ፣ ለመምታት መጋበዝ
   1.7. ህጋዊ ፍቃድ የሌላቸው ስብሰባዎችንና ምክክሮችን በግቢው ውስጥ ማካሄድ፣ መሳተፍ፣
   1.8. የራስ መታወቂያ ወይም የመመገቢያ ካርድን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት፣
   1.9. በሌላ ተማሪ መታወቂያ ወይም መመገቢያ ካርድ አገልግሎት ለማግኘት ማጭበርበር፣ ሲመገቡ መገኘት
   1.10. ለተማሪዎች የትራንስፓርት አገልግሎት ለመስጠት በሚደረገው እንቅስቃሴ በማንኛውም ስም ከተመን በላይ ማስከፈል፣ ለማስከፈል መሞከር፣ ለማስከፈል ማስተባበር መተባበር
   1.11. የአንድን ተማሪ መታወቂያ ወይም የመመገቢያ ካርድ ወይም ሌሎች ንብረቶችን ገንዘብ ወይም ሌሎች ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት በቅድመ ሁኔታነት መያዣ ማድረግ፣
   1.12. በተቋሙ ውስጥ የሚካሄድ አካዳሚያዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ማህበራዊ፣ ስፖርታዊ ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን መረበሽ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት መፈጸም፤

2. ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት የሚያስቀጡ የዲስፕሊን ጥፋቶች በዚህ ምድብ ይካተታሉ፡፡
   2.1. ሆን ብሎ የፈተና ወረቀት ሳያስረክብ ይዞ መውጣት፣ የሌላ ተማሪ የታረመም ሆነ ያልታረመ የፈተና ወረቀት ለማጥፋት መሞከር ወይም ማጥፋት ወይም መቅደድ፣
   2.2. በፈተና ወረቀቱ ላይ ስሙን ቀይሮ እንዲፈተንለት ሌላ ዲፓርትመንት ተማሪ ወይም ተማሪ ያልሆነ ሰው በራሱ ቦታ ማስፈተን፣
   2.3. አልኮልና ጫት ይዞ መግባት፣ ለመግባት መሞከር፣
   2.4. መታወቂያና መመገቢያ ካርድ ሳይጠፋበት ጠፋኝ በሚል አመልክቶ ሁለተኛ ለማግኘት መሞከር ወይም አግኝቶ በሁለት ካርድ ሲጠቀም መገኘት፣
   2.5. በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ የአምልኮ ቦታ መጠየቅ፣ ህንፃዎችን ለአምልኮ መጠቀም፣ በግቢው ውስጥ በቡድን ተሰባስቦ ሐይማኖታዊ ስርዓት ማካሄድ፣ መዘመር፣ መስገድ፣

2.6. በቤተ መጽሐፍት ወይም በሌሎች ክፍሎች ውስጥ ያሉ መጽሐፍትን፣ ጆርናሎችን ወዘተ ገጽ መቅደድና መገንጠል፣ ወይም መስረቅ

2.7. መረጃ በሌለበት በአሉባልታ፣ በመሰለኝና ባልታረጋገጠ ወሬ በስብሰባዎች ላይም ይሁን በሌሎች ሁኔቶች የዩኒቨርሲቲውን ኃላፊዎች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች ወይም ሌሎች ተማሪዎችን ማቃለል፣ የሃሰት ንግግሮችን በማድረግ ክብር መንካት፣ ስም ማጥፋትና የመሳሰሉ ድርጊቶችን መፈጽም፣

2.8. በክፍል ውስጥ፣ በዶርሚተሪ፣ በቢሮ ወይም በሌላ የዩኒቨርሲቲው ግቢ ክልል ውስጥ በስምምነት ላይ የተመሠረተ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ወይም ለመፈፀም መሞከር፣

2.9. የተማሪዎችን እንዲሁም የሌሎች አካላትን ንብረት መስረቅ ወይም መዝረፍ፣

2.10. በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባል ላይ የስነ-ልቦና ጉዳት ማድረስ፣ መሳደብ፣ ማስፈራራት፣ መዝለፍ፣ መረበሽ፣ ማስጨነቅ፣ እንዲሁም አእምሮውን፣ ማህበረሰባዊ ግንኙነቱን፣ ህይወቱን ወይም እንቅስቃሴውንና የስራ ሞራሉን ሊጐዱ የሚችሉ ሃይለ ቃሎችን መናገር፣ በሥራው ላይ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ማድረግ፣

2.11. ሳይታመም የታመመ በማስመሰል ከክሊኒክ መድኃኒት አውጥቶ ሲሸጥ ወይም ለሌላ ሰው ሲሰጥ መገኘት፣

2.12. መታወቂያ ካርዱን ወይም መመገቢያ ካርዱን፣ የቤተ-መጽሐፍት መዋሻ ካርድ ወይም ሌላ የግል መለያውን ለሌላ ተማሪ አሳልፎ በመስጠት ማስጠቀም ወይም ከሌላው ተቀብሎ መጠቀም፣

2.13. የሌላ ተማሪ መመገቢያ ካርድ፣ መታወቂያ ወይም ሌላ ዕቃ ሰርቆ ከወሰደ በኋላ እንዲመልስ ሲጠየቅ በገንዘብ ወይም በዓይነት ጥቅም ለማግኘት መደራደር ወይም ይህን ድርጊት ከሚፈጽም ሰው ጋር መተባበር፣

2.14. በሆቴሎች፣ በጭፈራ ቤቶች ወይም በሌሎች ቦታዎች በሴተኛ አዳሪነት ተሰማርቶ መገኘት ወይም እነዚህን የሚመስሉ ተግባራትን መፈጸም ወይም ይህን እንዲያደርጉ መገፋፋት፣ እንደአገናኝ ማገልገል፣

2.15. ያለግለሰቡ ፈቃድ ምስሉን ወይም ድምጹን በካሜራ ወይም በሞባይል ቀርፆ ለህዝብ ማሳየት ወይም ማሰማት፣ ለማንኛውም ተግባር እንዲውል ማድርግ፣

2.16. ለተማሪዎች ህብረት ስራ ማስኬጃ የተበጀተውን ገንዘብ ወይም የተማሪዎች ክበብ በድጋፍ ያገኘውን ወይም ከአባላት የተሰበሰበውን ገንዘብ የፋይናንስ የገቢና ወጭ ስርዓት ባልተከተለ መልኩ ማስኬድ፣ መመዝበር፣

2.17. ያለ ተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር እና ያለተማሪዎች ህብረት ፈቃድ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ በተመራቂ ተማሪዎች ኮሚቴም ሆነ በሌሎች ተማሪዎች አነሳሽነት ማንኛውም ተማሪ ብሔራዊም ሆኑ ብሔራዊ ያልሆኑ፣ ሐይማኖታዊም ሆኑ ሐይማኖታዊ ያልሆኑ በአላትን በቡድን ማክበር፣

2.18. በተማሪዎች ህብረት አባላት ላይ ሆን ብሎ ማመጽ፣ ችግር መፍጠር፣ ማዋከብ፣ ብሔራቸውን ወይም ሌሎች ማንነታቸውን መሠረት አድርጎ ማጣጣል፣ መስደብ፣ ሌሎች እንዲነሱባቸው መቀስቀስ፣ (ችግር ያለባቸውን ለይቶ በህጋዊ መንገድ እንዲነሱ በመረጃ ላይ የተደገፈ ጥያቄ ማቅረብ እንደተጠበቀ ሆኖ።)

2.19. በዩኒቨርሲቲ ሰራተኛ ወይም ተማሪ ላይ በማስፈራራት ወይም በመዛት የሆነ ነገር እንዲያደርግ ወይም እንዳያደርግ ማስገደድ፣

2.20. የዲሲፕሊን ጉዳይ የሚያይ የኮሚቴ አባልን፣ አመልካች ወይም ምስክር ሆኖ የቀረበ ሰውን፣ የተከሳሹን ወይም መከላከያ ምስክሮቹን ማስፈራራትና ውሳኔ እንዳይተላለፍ የማድረግ ሙከራ፣ ማጣራት በትክክልኛ መንገድ እንዳይካሄድ ማድረግ፣

2.21. ሐይማኖትን መሠረት በማድረግ ለራሱና ተከታዮቹ ልዩ መመገቢያ አዳራሽና ምግብ መጠየቅ፣ መመገቢያ አዳራሽ ውስጥ ከምግብ በፊትና በኋላ ፀሎት ሲያደርጉ ድምጽ ማሰማት፣ በቡድን ድምጽ እያሰሙ መጸለይ፣ ሌሎችን መረበሽ

2.22. ሐይማኖትን መሠረት በማድረግ ለራሱና ተከታዮቹ ልዩ የመመገቢያ ሰዓትና ምግብ በመጠየቅ ሁከት እንዲፈጠር ማድረግ፣

2.23. በተማሪዎች ህብረት አባልነት ስም ሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም፤

2.24. በዩኒቨርሲቲው በሚሰጡ ፈተናዎች ለሌላ ተፈታኝ ተማሪ ወይም አካል ሲፈተን መገኘት፣

2.25. የሌሎችን የፖለቲካ፣ የኃይማኖት፣ ብሄር፣ ቋንቋ፣ አመለካከት፣ ባህልና እምነት ማንቋሸሽ፣ ማንኳሰስ፣ የሃይማኖት መጽሐፍት ማበላሸት፣ ማቃጠል፣ የበዓላት ቀናትን አሳብቆ መረበሽ፣ ወዘተ፣

2.26. በሌሎች ተማሪዎች ወይም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባላት ላይ የሞራል ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ ትዕይንቶችን፣ እንቅስቃሴዎችን፣ ፊልሞችንና የመሳሰሉ ነገሮችን ማሳየት፣ ማቀነባበር ወይም ማሰራጨት፣

2.27. ሌሎች በዚህ ምድብ ሊካተቱ የሚችሉ የዲስፕሊን ጥፋቶች ተብለው በዩኒቨርሲቲው በጽሑፍ የሚለዩ ጥፋቶች፣

አንቀጽ 14፡- ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች፣

ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጡ (ከትምህርት ገበታ የሚያሳግዱ) የዲስፕሊን ጥፋቶች በዚህ ምድብ የሚካተቱ ይሆናል፡፡

1. የዩኒቨርሲቲውን ህግና ደንብ ለመጣስ፣ የአሰራር ስርአትና የሥራ አመራር ውሳኔ ለመቃወም ተማሪዎችን ለአድማ፣ ለአመጽና ለረብሻ ማነሳሳት፣ ማስተባበር፣ የሃሰት ወሬ መፍጠርና ማስፋፋት፣ ለህገ-ወጥ ሥራ ህብረት መፍጠር፣
2. በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይና በሌላ ቦታ ብጥብጥና ሁከት የሚያስከትል ያልተፈቀዱ ጽሁፎችን መለጠፍ፣
3. በአግባቡ በመካሄድ ላይ ባለ የዲሲፕሊን ጥፋት ክርክር የመሰማት ሂደት ላይ ጣልቃ መግባትና ማደናቀፍ፣ በስርዓቱ መሠረት ለመዳኘት የሚያመለክቱ ተማሪዎችንና ሠራተኞችን ማደናቀፍ፣ በዲስፕሊን ኮሚቴዎች ላይ ወከባ በመፍጠር በገለልተኝነታቸው ላይ ተፅዕኖ ለመፍጠር መሞከር፣
4. እንደ ማሪዋና፣ ካናቢስ፣ ሀሽሽ፣ ኮኬይን ወዘተ ያሉ ዕፆችን መጠቀም፤ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጭ ይዞ መገኘት ወይም በድብቅ ሲያዘዋውር ወይም ሲሸጥ መገኘት፣
5. ሀሳቡን በነፃነት የመግለጽ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ተማሪው የፖለቲካ ወይም የብሔር ምክንያቶችን በማንሳት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሰዎችን ለአመጽ ማነሳሳት፣
6. ለመምህርም ሆነ ለሌላ አካል ሆን ብሎ የሌላ ተማሪን የስራ ውጤት መደበቅ ወይም ማጥፋት
7. ገንዘብ ወይም ሌላ ዋጋ የሚያወጣ ነገር በመስጠት ያልተገባ የትምህርት ጥቅም ለማግኘት መሞከር፣
8. በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ በህዝብ ፊት ራቁትን መታየት፣

9. ዩኒቨርሲቲው በሚያወጣቸው ሕጎች ተገዢ ለመሆነ አለመፈለግ፣ ያለበቂ ምክንያት የትምህት ፕሮግራሞች እንዲቀየሩ አመጽ ማስነሳት፣ ሰላምን ማወክ፣ በተደጋጋሚ እንደማይለወጡ ተነገሮ ለመቀበል ዝግጁ አለመሆን፣
10. የሚኖርበትን ህንጻ አካባቢ፣ ዶርሚተሪ፣ ኮሪዶር፣ ሽንት ቤትና ሻወር እንዲያጸዳ ከጓደኞቹ ጋር ተመድቦ በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ኃላፊነቱን ለመወጣት እምቢተኛ ሆኖ መገኘት፣

አንቀጽ 15፡- በጣም ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች፣

ከዩኒቨርሲቲው የትምህርት መርሃ-ግብር ሙሉ በሙሉ መሰናበትን የሚያስከትሉ የዲስፕሊን ጥፋቶችን እንደሚከተለው ተመልክተዋል፡፡

1. ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶችን ፈጽሞ በተወሰደው እርምጃ መሻሻል ሳያሳይ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ፈፅሞ መገኘት፣
2. የሌሎችን ብሔር ወይም ኃይማኖት የሚጐዳ ድርጊት መፈፀም ለምሳሌ፡- መንፈሳዊ መጽሐፍት፣ ስዕሎችና ቅርፃቅርፆች፣ ሐይማኖታዊ ምልክቶች እንዲቃጠሉ ወይም ቅርፃቸው እንዲጠፋ ማድረግ፣
3. ድምጽ ባለው ወይም በሌለው መሣሪያ የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ አባል ሆነ ከዩኒቨርሲቲው ውጭ ያሉ የማህበረሰብ አባላትን መጉዳት ወይም ለመጉዳት ሙከራ ማድረግ፣
4. በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ሊያስከትሉ የሚችሉ ስለታማና ተተኳሽ መሳሪያዎች ወይም መርዛማ ነገሮችን ይዞ መገኘት፣ ለመግባት መሞከር
5. አስገድዶ መድፈር ወይም የተቃራኒ ፆታውን የመከላከል አቅም በጉልበት ወይም በስነ-ልቦና ጫና በማድከም ፆታዊ ጥቃት ማድረስ ወይም ለማድረስ መሞከር፣ በጉልበት ገፍቶ ወደ ተቃራኒ ፆታ መኝታ ቤት መግባት፣፣
6. በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ሆን ብሎ ወይም በቸለልተኝነት ወይም በጥንቃቄ ጉድለት ቃጠሎ ለማስነሳት መሞከር ወይም ማስነሳት፣
7. በተጭበረበረ የትምህርት ማስረጃ ተመዝግቦ መገኘት፣
8. ፌርማን መኮረጅ ወይም ሰነድን መደለዝ፣ በመሰረዝ ማጭበርበር፣ ለማጭበርበር መሞከር፣
9. በማስፈራራትና ጉልበት በመጠቀም የሌላ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ንብረት መውሰድ ወይም ለመውሰድ ሙከራ ማካሄድ (ዘረፋ መፈፀም)፣
10. ተገቢውን ክፍያ ሳይፈጽም ወይም የወጭ መጋራት ውል ሳይፈርም መማር ወይም የአገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን መሞከር፣
11. የሌሎች ተማሪዎችን ዓላማና ህይወት በሚያሰናክል ህገ-ወጥ እንቅስቃሴ ላይ ተሰማርቶ መገኘት ለምሳሌ ያልተፈቀዱ የጭፈራ ሥርዓቶችንና በዓላትን በግቢው ውስጥም ሆነ ውጭ ማዘጋጀት፣ ተባባሪ መሆን፣ ለዝሙት ማቃጠር፣ ማሻሻጥ፣ ሀሽሽና ሌሎች አደንዛዥ እጾችን ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች እንዲጠቀሙ ማበረታታት፣ ወዘተ
12. ተመሳሳይ ጾታ ጋር ግንኙንት መፈጸም፣ ያልሆኑ ከባህል ያፈነገጡ ነገሮችን ሲያደርጉ መገኘት፣
13. የሌላ ተማሪን ቋንቋ፣ ብሔር፣ ሐይማኖት እና ማንነት ማንቋሸሽ፣
14. ተማሪው ባገኘው ውጤት ቅር በመሰኘት በመምህሩና በመምህሩ ቤተሰብ ላይ ጉዳት ለማድረስ መሞከር ወይም ማድረስ፣

15. በመመገቢያ አዳራሽ አካባቢ ከምግብ ጋር አያይዞ ወይም በየትኛውም ምክንያት ዓመጽ ማስነሳት ወይም ለማስነሳት መሞከር፣ በስራ ላይ ያሉ ስራተኞችን መደባደብ፣
16. ጉበዝ ተማሪዎችን በጉልበት በማስፈራራት እንዲያሰቀዱ ማስገደድ፣ ፈተና ክፍል ወስጥ ሁከት መፍጠር፣
17. ሌሎች ከነዚህ ጋር ይመሳሰላሉ ብሎ ዩኒቨርሲቲው የሚጨምራቸው የዲስፕሊን ጥፋቶች

አንቀጽ 16፡- እጩ ምሩቃን የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽመው ሲገኙ የሚወሰዱ እርምጃዎች

የመጨረሻውን የመመረቂያ የትምህርት ዓመት ፈተና ተፈትነውና ትምህርታቸውን አጠናቀው ለመመረቅ የተዘጋጁ እጩ ምሩቃን የዩኒቨርሲቲውን ህግ ወይም የስነ-ምግባር ደንቦች በማክበር በኩል ለሌሎች ተማሪዎች አርአያ ሆነው መገኘት ሲገባቸው አልፎ አልፎ ቀላል ወይም ከባድ የስነ-ምግባር ጥፋቶችን ሊፈጽሙ ይችላሉ። ጥፋት ፈጽመው ሲገኙ ከሚጠብቃቸው ሃገራዊ ኃላፊነት አንፃር ሲታይ ያልተገባ በመሆኑ የጥፋታቸው ክብደት እየተመረመረ የዲስኘሊን እርምጃ በሚከተለው አግባብ እንዲወሰድ ይደረጋል።

ማንኛውም እጩ ምሩቅ፡-

1. አነስተኛ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ ከሁለት እስከ ስድስት ወራት ማንኛውም ዓይነት የትምህርት ማስረጃ ይያዝበታል።
2. ቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ ከሰባት ወራት እስከ ዘጠኝ ወራት የትምህርት ዓመት ማንኛውም ዓይነት የትምህርት ማስረጃ ይያዝበታል።
3. መካከለኛ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ ከአስር እስከ አስራ አምስት ወራት ማንኛውም ዓይነት የትምህርት ማስረጃ ይያዝበታል፣
4. ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ ከአስራ ስድስት ወራት እስከ ሁለት ዓመት ማንኛውም ዓይነት የትምህርት ማስረጃው ይያዝበታል፣
5. በጣም ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ የትምህርት ማስረጃው በጭራሽ አይሰጥም።

አንቀጽ 17፡- በተማሪ ውክልና የተለያየ ኃላፊነት ያለባቸው ተማሪዎች የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽመው ሲገኙ የሚወሰዱ እርምጃዎች

1. የተማሪዎች ህብረት አባል፣ የክበብ መሪ፣ የክፍል ተወካይ፣ የብሎክ ተወካይ፣ የፍሎር ተወካይ፣ የዶርም ተወካይ ወይም በሌሎች በማንኛውም መንገድ የተማሪ ተወካይ ሆኖ ሲሰራ ተማሪዎች እኩል እንዳይሳተፉ በዘር፣ በብሔር፣ በሐይማኖት፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካዊ አመለካከት፣ ወዘተ ላይ የተመሰረተ አድሎ የፈፀመ ከሆነና በማስረጃ ከተረጋገጠ ወዲያውኑ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከተሰጠው ኃላፊነት እንዲነሳ ይደረጋል፣
2. ከላይ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀውን ቢኖርም በዚህ መመሪያ ቅጣት የተቀመጠለትን የዲሲፕሊን ጥፋት የሚፈጽም የህብረቱ አባል ወይም የክበቡ መሪ ወይም ማንኛውም የተማሪ ውክልና ኃላፊነት ያለበት ተማሪ እንደማንኛውም ተማሪ በመመሪያው መሠረት ይጠየቃል።

አንቀጽ 18፡- የየዲስፕሊን ጥፋት ቅጣት ዓይነቶች

በዚህ መመሪያ መሠረት የዲስፕሊን ጥፋት በፈጸመ ተማሪ ላይ ሊወሰድ የሚችል ቅጣትና እርምጃ፡-

ሀ. የቃል ግሳጼ፤ በጽሑፍ የሚሰጥ የቃል ማስጠንቀቂያ
ለ. የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ

ሐ. ስለ ጉዳዩ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች ማሳወቅ
መ. ማህበራዊ አገልግሎት የሚያሰጥ ቅጣት፣
ሠ. ጥፋት የፈፀመበትን ንብረት መውረስ
ረ. በዲስፕሊን ጥሰቱ የተጎዱ ወይም ዋጋቸው የቀነሰ፣ ወይም ሙሉ በሙሉ የወደሙ ንብረቶች ወይም ሕንፃዎች፣ ተገጣጣሚዎች ካሉ የሚተኩ ከሆኑ እንዲተኩ ማድረግ፣ ካልሆነ ዩኒቨርሲቲው በባለሙያ አስጠንቶ በሚያቀርበው የወቅቱ የገበያ ዋጋ መሠረት ዋጋውን ማስከፈል
ሰ. የተወሰደ ንብረት ካለ ማስመለስ፣ ከልሆነ የወቅቱን የገበያ ዋጋ ግምት በመንግስት ንብረት ህግ መሠረት በገንዘብ እንዲከፈል ማድረግ
ሸ. ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርት ማገድ
ቀ. ሙሉ በሙሉ ከትምህርት ማሰናበት
በ. የትምህርት ማስረጃውን ለተወሰነ ጊዜ መያዝ
ተ. የትምህርት ማስረጃ ፈጽሞ አለመስጠት
ቸ. ጉዳዩን በወንጀል ወይም በፍታብሔር ሕግ እንዲታይ ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ

ክፍል ስድስት

የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ

አንቀጽ 19፡- የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ ስለማቋቋም

የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ በየደረጃው በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት የሚቋቋም ነው፡፡

ሀ. በትምህርት ክፍል ደረጃ
ለ. በኮሌጅ ወይም በፋኩልቲ ወይም በኢንስቲትዩት ደረጃ
ሐ. ከላይ በ(ሀ)ና (ለ) ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዩኒቨርሲቲው ፈጣን፣ ጥራት ያለውና ፍትኃዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ሆኖ ካገኘው ለዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት ተጠሪ የሆነ የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ወይም በከምፓስ ደረጃ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

አንቀጽ 20፡- የዲስፕሊን ኮሚቴው ተጠሪነት

ሀ. በትምህርት ክፍል ደረጃ የተቋቋመ የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለኮሌጅ ወይም ለፋኩልቲ ወይም ለኢንስቲትዩት ዲን/ኃላፊ ይሆናል፡፡
ለ. በኮሌጅ ወይም በፋኩልቲ ወይም በኢንስቲትዩት ደረጃ የተቋቋመ የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት ይሆናል፡፡
ሐ. ከዋና ከምፓስ ወጪ ባሉ ቅርጫፍ ከምፓስ (ሶች)
   i. በትምህርት ክፍል ደረጃ የተቋቋመ የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለኮሌጅ ወይም ለፋኩልቲ ወይም ለኢንስቲትዩት ዲን ይሆናል፡፡
   ii. በኮሌጅ ወይም በፋኩልቲ ወይም በኢንስቲትዩት የተቋቋመ የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ ተጠርነቱ ለከምፓሱ አስተዳደር ዲን ይሆናል፡፡

ስለሆነም ኮሚቴው ማንኛውንም የዲስፕሊን የውሳኔ ሐሳብ ተጠሪ ለሆኑበት አካላት በማቅረብ ያስጸድቃል፡፡

አንቀጽ 21፡- **የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ አባላት**

ስብጥሩም ከመምህራን፣ ከተማሪዎች ህብረትና እንደአስፈላጊነቱ ከአስተዳደር ሠራተኞች የተውጣጡ አባላት ያሉት ይሆናል።

1. በትምህርት ክፍል ደረጃ የሚቋቋመው የዲስፕሊን ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል።
   እነርሱም፡-
   ሀ. ከትምህርት ክፍሉ አንድ ነባር መምህር .....ሰብሳቢ
   ለ. የትምህርት ክፍሉ ሁለት የተማሪዎች ተወካዮች (አንድ ወንድና አንድ ሴት)--አባል
   ሐ. የትምህርት ክፍሉ የመምህራን ማህበር ተወካይ.....አባል
   መ. ከትምህርት ክፍሉ አንድ የአስተዳደር ሠራተኛ.....አባልና ፀሐፊ

2. በኮሌጅ ወይም በፋኩልቲ ወይም በኢንስቲትዩት ደረጃ የዲስፕሊን ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል።
   እነርሱም፡-
   ሀ. ከኮሌጅ ወይም ከፋኩልቲ ወይም ከኢንስቲትዩት አንድ ነባር መምህር .....ሰብሳቢ
   ለ. የኮሌጅ/የፋኩልቲ/የኢንስቲትዩት ሁለት የተማሪዎች ህብረት ተወካዮች (አንድ ወንድና አንድ ሴት).....አባል
   ሐ. ከኮሌጅ ወይም ከፋኩልቲ ወይም ከኢንስቲትዩት የመምህራን ማህበር ተወካይ--አባል
   መ. ከኮሌጅ/ከፋኩልቲ/ከኢንስቲትዩት አንድ የአስተዳደር ሠራተኛ.....አባልና ፀሐፊ

3. ከላይ በ1ና በ2 የተገለጹትን የኮሚቴ አባላት አሰያየም በተመለከተ
   ሀ. የትምህርት ክፍል የተማሪዎች ዲስፕሊን ኮሚቴ አባላትን የትምህርት ክፍሉ ካውንስል (Department Council (DC)) መርጦ ሰብሳቢ፣ ም/ሰብሳቢ፣ ፀሐፊና አባላት ብሎ ለይቶ በፋኩልቲው አካደሚክ ኮሚሽን (Academic Comission (AC)) አስጸድቆ ለፕሬዚዳንት ያቀርባል።
   ለ. የኮሌጅ ወይም የፋኩልቲ ወይም የኢንስቲትዩት የተማሪዎች ዲስፕሊን ኮሚቴ አባላትን የፋኩልቲው አካደሚክ ኮሚሽን (Academic Comission (AC)) መርጦ ሰብሳቢ፣ ም/ሰብሳቢ፣ ፀሐፊና አባላት ብሎ ለይቶ ለፕሬዚዳንት ያቀርባል።
   ሐ. ከላይ በ3 በ(ሀ)ና (ለ) ላይ በተገጸው መሠረት የቀረቡትን የኮሚቴ አባላት ፕሬዚዳንቱ ተቀብሎ ሊያጸድቅ ወይም ሊቀይር ይችላል።

አንቀጽ 22፡- **የተማሪዎች ዲስፕሊን የኮሚቴ አባላት የሚከተሉትን ሊያሟሉ ይገባል**

ሀ. በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በስነ-ስርዓት አክባሪነታቸው፣ በታማኝነታቸውና በቁርጠኝነታቸው የሚታወቁና ፍትሃዊና ሚዛናዊ እይታ ያላቸው፤ የማያዳሉ፤
ለ. በዲስፕሊን ጥፋት ተከሰውና ተቀጥተው የማያውቁ
ሐ. በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በአብዛኛው ወገን ተቀባይነት ያላቸው
መ. በዩኒቨርሲቲው ቢያንስ የአንድ ዓመት ቆይታ ያላቸው
ሠ. ከላይ ከ(ሀ) እስከ (መ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ ዩኒቨርሲቲ/ካምፓስ ሲቋቋም የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት የሚወስን ይሆናል።

አንቀጽ 23፡- **የኮሚቴው ሥልጣን**

ሀ. ኮሚቴው የቀረበለትን የተማሪዎችን የዲስፕሊን ጥፋት ክስ በዚህ መመሪያ መሠረትና ሌሎች በተማሪዎቹ ላይ ተፈፃሚነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮ የውሳኔ ሐሳብ አንቀጽ 20 መሠረት ያቀርባል።

ለ. በትምህርት ክፍል ዲስፕሊን ኮሚቴ ታይቶ ውሳኔ ያገኘን ጉዳይ ለኮሌጁ/ለፋኩልቲው/ለኢንስቲትዩቱ የዲስፕሊን ኮሚቴ በይግባኝ የቀረበ ከሆነ መርምሮ የውሳኔ ሃሳቡን ለአስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት ያቀርባል፡፡

ሐ. ክሱን በሚመለከት ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም የሥራ ክፍል መረጃው ጠይቆ የመውሰድ፣ ማንኛውንም አካል አስቀርቦ የመመርመር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ የሥራ ክፍሎችም የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

አንቀጽ 24፡- የኮሚቴው አባላት መጓደል

ከኮሚቴው ውስጥ አንድ አባል የተጓደለ ከሆነ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት እንዲያውቀው ተደርጎ በኮሚቴው ሰብሳቢ አቅራቢነት ተጠሪ የሆኑበት የቅርብ ኃላፊ ተተኪ ይመድባል፡፡ ከአንድ በላይ አባል ከሆነ ግን በአንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ይፈጸማል፡፡

አንቀጽ 25፡- ከኮሚቴ አባልነት ስለመነሳት

ሀ. የኮሚቴው ሰብሳቢ ከሳሽ በሚሆንበት ጊዜ በአባላቱ ውሳኔ መሠረት ከአባላቱ መካከል አንዱ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

ለ. የኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም ማንኛውም አባል ክስ ከቀረበበት ተማሪ ጋር የግል ጠብ ወይም የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ለዚህ ጉዳይ ብቻ በጊዜያዊነት ከሰብሳቢነቱ ወይም ከአባልነቱ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

ሐ. ማንኛውም የኮሚቴ አባል ራሱን ከጉዳይ በማግለል በሌላው አባል ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር ወይም ችግር ውስጥ ለማስገባት ከባለጉዳይ ጋር እየተገናኘ ሚስጢር ያወጣ ወይም ቃለ ጉባኤዎችን፣ መረጃዎችንና ጽሁፎችን ለባለጉዳይ ያሳየ ወይም የገለጸ ወይም የሰጠ እንደሆነ ከአባልነቱ ይነሳል፣ በከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋትም በአባላቱ ወይም በሰብሳቢው ይከሰሳል፤ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

መ. ማንኛውም የኮሚቴ አባል በተደጋጋሚ ያለ ማንም ፈቃድ የኮሚቴ ስብሰባ ጥሪ ሲደረግ የሚቀር ከሆነ የጽሑፍ ማብራሪያ እንዲያቀርብ ይደረጋል፤ ጉዳዩም በፋይሉ ውስጥ እንዲያያዝ ይደርግና ከአባልነቱ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡ በዲስፕሊን ጥፋትም ሊጠየቅ ይችላል፡፡

አንቀጽ 26፡- የኮሚቴው ምልዓተ ጉባኤና ድምጽ አሰጣጥ፣

ሀ. በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ግማሽ (50%) አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ሙሉ ይሆናል፡፡

ለ. አከራካሪ ጉዳይ ሲያጋጥም የኮሚቴው አስተያየት የሚያልፈው በድምጽ ብልጫ ሲሆን እኩል በኩል ከሆነ ሰብሳቢው ባለበት ወገን የቀረበው ሃሳብ ይፀድቃል፤ በሃሳብ የተለየ አባል ካለ የተለየበት ምክንያት በቃለ ጉባኤው ላይ ይሰፍራል፡፡

ሐ. ሰብሳቢው የክስ ሂደቱን በአግባቡ መምራት አለበት፡፡ በክርክሩ ወቅት አንድ የኮሚቴ አባል የስነ-ምግባር ግድፈት ካሳየ ከስብሰባው በጊዜያዊነት እንዲወጣ ማድረግ ይችላል፡፡ ይህ ምልዓተ ጉባኤውን ሊያጎል የሚችል ከሆነ አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲያውቀው በማድረግ የጎደለው አባል እንዲተካ ወይም ባሉት አባላት ውሳኔ እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

መ. ማንኛውም የኮሚቴው አባል በስብሰባው ኖረም አልኖረም የሃሳብ ልዩነት ኖረውም አልኖረውም በቃለ ጉባኤው ላይ ይፈርማል፣

አንቀጽ 27፡- የኮሚቴው የስብሰባ ጊዜና የአባላት ሰዓት አከባበር

ሀ. ኮሚቴው የሚሰበሰብበትን ቀንና ሰዓት እንደየክሱ ጉዳይ አንገብጋቢነትና ብዛት እየታየ በኮሚቴው ሰብሳቢ ይወሰናል። ቢያንስ ከአንድ ቀን በፊትም ለአባላቱ አመቺ በሆነ መንገድ የሚገለጽ ይሆናል።

ለ. ማንኛውም የኮሚቴው አባል አስቀድሞ ሰብሰቢውን ሳያስፈቅድ፣ አሳማኝ ባልሆነ ሰበብ አስባብ ለተደጋጋሚ ቀናት ቢቀር ወይም ስብሰባውን ቢያስተጓጉል ሰብሳቢው በሚያቀርበው ማስረጃ መሠረት በአስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት (ለመምህራን በአካዳምክ ም/ፕሬዚዳንት) በኩል ተገቢው አስተዳድራዊ እርምጃ ይወሰድበታል።

አንቀጽ 28፡- የዲስፕሊን ኮሚቴው የስራ ዘመን

የኮሚቴው የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል። ሆኖም አባላት እንደገና ተመርጠው ለሁለት ዙር ብቻ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

ክፍል ሰባት
የሥነ-ስርዓት ድንጋጌዎች

አንቀጽ 29፡-የዲስፕሊን ጥፋት ክስ አመሠራረት

1. ማንኛውም ከመማር ማስተማር ጋር የተያያዙ ጥፋቶችን ተማሪዎች ፈጽመው ሲገኙ ተማሪው የተመዘገበበት የትምህርት ክፍል ኃላፊ በጽሑፍ የተደራጀ ክስ ይመሰርታል። ይህም ከምዘናና ከፈተና አስተዳደር፣ ከቤተ መጽሐፍት፣ ከሪጅስትራር፣ ከመማሪያ ክፍል፣ ከዩኒቨርሲቲ ውስጥና ከዩኒቨርሲቲ ውጭ ባሉ ቤተ ሙከራዎች፣ በመስክ ላይ በሚደረግ የተግባር ትምህርትና ልምምድ፣ ከዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር፣ ከመምህራን፣ ከወርክሾፕና ከላቦራቶሪ ሠራተኞች ጋር በተገናኘ እና መሠል ከመማር ማስተማሩ ጋር ተያያዥ የሆኑ ዲስፕሊን ጥፋቶችን ያካትታል።
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት ውጭ ያሉት ማንኛቸውም ጥፋቶች በተማሪዎች ተፈጽመው ሲገኙ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ተደርገው ተወስደው የተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር ክስ ይመሰርታል።
3. በዚሁ መሠረት፡-
   3.1. አነስተኛና ቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ሆኖ ክስ የሚመሠረት ከሆነ ክሱ ለትምህርት ክፍል ተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ ይቀርባል።
   3.2. መካከለኛ፣ ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋት ከሆነ ክሱ ለለኮሌጅ/ፋኩልቲ/ኢንስቲትዩት ተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ ይቀርባል።

አንቀጽ 30፡- የዲስፕሊን ጥፋት ክስ አቀራረብ

ማንኛውም የዲስፕሊን ጥፋት ክስ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች ተከትሎ ይቀርባል።

1. ማንኛውም የዲስፕሊን ጥፋት ክስ በጽሑፍ ይቀርባል።
2. የዲስፕሊን ጥፋት የክስ ጽሑፍ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።
   ሀ. የከሳሹን ስም፣ ፊርማና አድራሻ እንዲሁም ክሱ የተመሰረተበት ቀን
   ለ. የተከሳሽ ተማሪ ስም፣ መለያ ቁጥር፣ ዲፓርትመንት፣ የትምህርት ዓመት
   ሐ. የዲስፕሊን ጥፋቱ የተፈፀመበትን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት
   መ. የዲስፕሊን ጥፋቱን ዝርዝር ማብራሪያ
   ሠ. የተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋቱ ደረጃ
   ረ. የማስረጃዎች ዝርዝር (ምስክር/አማኝ ካለ ስምና አድራሻ እንዲሁም የጽሑፍ) ከሞናው ጋር የተመሳከረ ቅጂ በማያያዝ

ሰ. ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ (ካለ)

ረ. ተማሪው ከአንድ በላይ በሆነ የዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰ ከሆነ ለእያንዳንዱ ጥፋት ተለይቶ ከላይ (ሀ)- (ሰ) በተመለከተው መሠረት መቅረብ አለበት።

ሸ. በጋራ እና ተመሳሳይ ጥፋት የተሳተፉ ከሆነ በጣምራ ሊከሰሱ ይችላሉ።

አንቀጽ 31፡- ክስ መመስረቻ ጊዜ

ሀ. የዲስፕሊን ጥፋቱ ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፤

ለ. የዲስፕሊን ጥፋቱ አነስተኛ ከሆነና ለዲስፕሊን ኮሚቴ መቅረብ የሌለበት ከሆነ ሥልጣን የተሰጠው አካል ጥሰቱ በተፈጸመ በ3 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ እርምጃ ወስዶ ያሳውቃል።

ሐ. ከላይ በ(ሀ)ና በ(ለ) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ መሠረት ያልተፈጸመ ከሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አካላት በየትኛውም ጊዜ ጉዳዩን ማንቀሳቀስ ይችላሉ።

አንቀጽ 32፡- ክስን ስለማሻሻል

ሀ. በዲስፕሊን ጥፋት የክስ ጽሁፍ ውስጥ የተገለጸው ጥፋት ዝርዝር በሚመለከት መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ስህተት ወይም ግድፈት መኖሩ ሲታወቅ የውሳኔ ሐሳብ ከመቅረቡ በፊት በማናቸውም ጊዜ ክሱን ማሻሻል ይቻላል።

ለ. በንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት የዲስፕሊን ክሱ ሊሻሻል የሚችለው በክሳሹ አነሳሽነት ወይም ክሱን በሚያጣራው የዲስፕሊን ኮሚቴ ጥያቄ መሠረት ሊሆን ይችላል።

አንቀጽ 33፡- ክስ ስለማቋረጥ

ሀ. የዲስፕሊን ጥፋት ክስ የቀረበበት ተማሪ በሞት ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ከዩኒቨርሲቲው ጋር ያለው ግንኙነት ሙሉ በሙሉ የተቋረጠ እንደሆነ ክሱ መታየት ያቆማል።

ለ. ነገር ግን መካከለኛና ከዚያ በላይ የዲስፕሊን ጥፋት የፈጸመ ተማሪ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ለመማር የተመዘገበ ከሆነ ክሱ መታየቱን ይቀጥላል። ውሳኔውም ለመማር ወደተመዘገበበት ዩኒቨርሲቲ ለአፈጻጸም ይላካል። ተማሪው የተመዘገበበትና ውሳኔውን የሚፈጽም ተቋም በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔውን ያስፈጽማል፤ ያልተረዳው የግንዛቤ ጉዳይ ካለ ውሳኔውን ያሳለፈውን ተቋም ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል።

ሐ. ከውሳኔ በፊት የዲስፕሊን ክስ የተመሠረተበት ተማሪ ዝውውር አይፈቀድም።

አንቀጽ 34፡- ክስን ስለማሳወቅ

ሀ. የዲስፕሊን ኮሚቴ ክስ የቀረበበት ተማሪ መልሱን ይዞ እንዲቀርብ የክሱን ጽሑፍና ማስረጃዎች ቅጅ አባሪ በማድረግ የክስ ማስታወቂያ አስፈርሞ ይሰጠዋል።

ለ. የክስ ማስታወቂያው ክሱ የሚሰማበትን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት የሚገልጽ ሆኖ ክሱ ከሚሰማበት ቀን ቢያንስ ከሶስት የሥራ ቀናት በፊት ለተከሳሹ ተማሪ መድረስ አለበት።

ሐ. ተማሪው ሊገኝ ባለመቻሉ ወይም ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ የክስ ማስታወቂያውን ለመስጠት ያልተቻለ እንደሆነ ምግብ ቤት አዳራሽ፣ መኖሪያ ሕንፃና ቤተመጽሐፍት

ሕንፃ እና በግልጽ በሚታይ የዩኒቨርሲቲው የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ ለአምስት ተከታታይ ቀናት እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

አንቀጽ 35፡- የክስ መልስ ስለማቅረብ

ሀ. ተከሳሽ የክስ መልሱን ማቅረብ ያለበት በጽሑፍ ነው፡፡

ለ. ተከሳሽ ተማሪ የተከሰሰበት ጉዳይ፡-

1. በዲስፕሊን ጥፋት የማያስከስሰው ከሆነ ወይም
2. ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ ክሱ ሊታይ አይገባውም የሚል የክስ መቃወሚያ የማቅረብ መብት አለው፡፡
3. ከላይ (1) እና (2) መሠረት የቀረበውን መቃወሚ የዲስፕሊን ኮሚቴው የተቀበለው እንደሆነ ክሱ እንዲቋረጥ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡ መቃወሚያውን ያልተቀበለው ከሆነ በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተማሪ ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ ያዘዋል፡፡

ሐ. የዲስፕሊን ክስ የቀረበበት ተማሪ ክሱን በማመን ወይም በመካድ መልሱን ማቅረብና ሲጠራም በአካል በመቅረብ ለዲስፕሊን ኮሚቴው ስለጉዳዩ ማስረዳት ይኖርበታል፤

መ. የክስ መልሱ በክሱ ለተጠቀሰው ለእያንዳንዱ የዲስፕሊን ጥፋት የተሰጠውን ምላሽና ተከሳሹ የሚፈልጋቸውን የመከላከያ ማስረጃዎችን ዝርዝር የያዘ ሊሆን ይገባል፡፡

ሠ. የክስ መልሱ ተከሳሽ ከዘረዘራቸው የመከላከያ ማስረጃዎች መካከል በእጁ የሚገኙትን የጽሑፍ ማስረጃዎችን ቅጅ የያዘና የዲስፕሊን ኮሚቴው እንዲያስቀርብለት የሚጠይቃቸውን ማስረጃዎች የትና በማን እጅ እንዳሉ በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡

ረ. በዲስፕሊን የተከሰሰ ተማሪ የመከላከያ ማስረጃዎችን አቅርቦ የማሰማት መብት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ቅረብ በተባለበት ዕለትና ሰዓት ባይቀርብ በቀረቡት ሪፖርቶችና ማስረጃዎች ላይ መሰረት ተደርጎ የቅጣት ውሳኔ ይተላለፍበታል፡፡

ሰ. በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተማሪ በማመን መልስ የሰጠ እንደሆነ ተጨማሪ ማጣራት አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ክሱን ከዚህ መመሪያ ጋር በማገናዘብ የውሳኔ ሐሳብ ይቀርባል፡፡

ሸ. በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተማሪ በመካድ መልስ የሰጠ እንደሆነ ኮሚቴው የሁለቱንም ወገን ምስክሮች በመስማትና ሌሎች ማስረጃዎችን በመመርመር አጣርቶ የውሳኔ ሐሳቡን ያቀርባል፡፡

አንቀጽ 36፡-ምስክር ስለመጥራት

ሀ. የዲስፕሊን ኮሚቴው ምስክሮች ከሚፈለጉበት አንድ ቀን ቀደም ብሎ ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ መጥሪያ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡

ለ. በአንድ የዲስፕሊን ጥሰት ላይ የሚመሰክሩ ምስክሮች በአንድ ጊዜ ተጠርተው ተራ በተራ በኮሚቴው ፊት ቀርበው እንዲመሰክሩ ይደረጋል፡፡

ሐ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ምስክሮችን ከሳሹ ወይም ኮሚቴው ሊያቀርቡና ምስክርነታቸውም ሊሰማ ይችላል፡፡

አንቀጽ 37፡- የምስክር ቃል ስለመስማት

ሀ. ምስክሮች ሲሰሙ በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተማሪና ክሱን ያቀረበው አካል ሁለቱም በተገኙበት ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን አንዱ ወገን ተነግሮት የቀረ እንደሆነ የምስክሮቹን ቃል ከመቀበል አያግድም፡፡

ለ. የምስክሮቹ መልስ ቃል በቃል የሚመዘገብ ይሆናል፡፡

ሐ. ተከራካሪ ወገኖች የቀረቡ ምስክሮችን ተጨማሪ ወይም መስቀለኛ ጥያቄዎችን መጠየቅና ይህም እንዲመዘገብላቸው ማድረግ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ 38፡- በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰው ተማሪ የመጨረሻ ቃል

የዲስፕሊን ኮሚቴው የዲስፕሊን ጥፋቱን የማጣራት ሥራ ከማጠናቀቁ በፊት ተከሳሹ ተማሪ የመጨረሻ ሐሳቡን በተከሰሰበት ጉዳይ ላይ እንዲናገር ዕድል ይሰጠዋል፡፡ ይህም ቃል በቃል ይመዘገባል፡፡ በቅጣት አወሳሰንም ለቅጣት ማክበጃነት ወይም ማቅለያነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

አንቀጽ 39፡-የውሳኔ ሐሳብ ስለማቅረብ

ሀ. የተማሪዎች ዲስፕሊን ኮሚቴ የዲስፕሊን ጥፋቱን አጣርቶ እንዳጠናቀቀ ወዲያውኑ የምርመራውን ውጤትና ሊወሰድ የሚገባውን የዲስፕሊን እርምጃ የሚያመላክት የውሳኔ ሐሳብ ፊርሞ ተጠሪ ለሆነበት ኃላፊ (ትምህርት ክፍል ዲስፕሊን ኮሚቴ ከሆነ ለኮሌጅ/ ፋኩልቲ/ ኢንስቲትዩት ዲን ያቀርባል፤ የኮሌጅ/ፋኩልቲ/ ኢንስቲትዩት ኮሚቴ ከሆነ ለአስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት) ያቀርባል፡፡

ለ. የኮሚቴው የውሳኔ ሐሳብ የሚከተሉትን ሊይዝ ይገባል፤

- የተማሪውን ሙሉ ስም፣ መለያ ቁጥር፣ ትምህርት ክፍል፣ የትምህርት ዓመት፣ የሚኖርበት ሕንጻና ዶርም ቁጥር፣
- የተማሪውን የትምህርት ውጤት
- የተማሪውን የቀድሞ ሪከርድ
- የዲስፕሊን ጥፋቱን ዝርዝር፣ ደረጃና የተፈጸመበትን ሁኔታ
- የተከሳሽ ምላሽ
- የምስክሮችን ቃል፣
- ዝርዝር የውሳኔ ሐሳብ
- የኮሚቴው አባላት ፊርማ ያለበት ቃለ ጉባኤ ከነአባሪ ማስረጃዎች ጋር
- የሰብሳቢው ፊርማ ያለበት ሽኚ ደብዳቤ

ሐ. በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰ ተማሪ ተጣርቶ ከተከሰሰበት ጉዳይ ነጻ መሆኑ ሲረጋገጥ ይህንኑ የሚገልጽ የጽሑፍ መረጃ ይሰጠዋል፡፡

አንቀጽ 40፡- የአስተዳደር ፕሬዚዳንት ውሳኔ

የዩኒቨርሲቲው ኮሌጅ/ፋኩልቲ/ኢንስቲትዩት ዲን ወይም አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ በዚህ መመሪያ መሠረት ከመረመረ በኋላ ፡-

ሀ. የኮሚቴውን የውሳኔ ሐሳብ ሙሉ በሙሉ የማጽደቅ

ለ. ኮሚቴው ያቀረበውን የውሳኔ ሐሳብ የማሻሻል

ሐ. ኮሚቴው ጉዳዩን እንደገና እንዲመረምር ምክንያቶችን ገልጾ የማዘዝ ሥልጠን አለው፡፡

በዩኒቨርሲቲው ኮሌጅ/ፋኩልቲ/ኢንስቲትዩት ዲን ወይም በአስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንቱ የጸደቀው የዲስፕሊን ውሳኔ ለተማሪው በጽሑፍ ይሰጠዋል፤ ከከባድ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እና ከዚያ በላይ የዲስፕሊን እርምጃ የተወሰደበት ከሆነ ተመሳሳይ ቅጂ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ባሉ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ ይለጠፋል።

አንቀጽ 41፡-የውሳኔ አፈጻጸም

ሀ. የዲስፕሊን እርምጃ ውሳኔ ከጸደቀበት ቀን አንስቶ ተፈጻሚ ይሆናል። ሆኖም ግን ተማሪው ከዩኒቨርሲቲው ግቢ የሚወጣ ከሆነ የ24 ሰዓታት ጊዜ ይሰጠዋል። ይህም ማለት የተማሪነት መብቱን ማጣትን እንጂ እንደ አንድ ባለጉዳይ ከውጪ እየተመላለሰ መጨረስ ያለበት ጉዳይ ካለ የሚመለከተውን አካል አስፈቅዶ መጨረስ ይችላል።

ለ. በንዑስ አንቀጽ (ሀ) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩን ይግባኝ ብሎ ይግባኙ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ጥያቄ አቅርቦ ከተፈቀደለት በግቢ ውስጥ ሆኖ እየተማረና አገልግሎት እያገኘ ጉዳዩን መከታተል ይችላል።

አንቀጽ 42፡- የተማሪዎች የዲሲፕሊን ጉዳይ ሰሚ ኮሚቴ የክስ አሰማም ሂደት (ስነ-ስርዓት)

1. ሰብሳቢው የኮሚቴውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል። ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ምክትሉ ኃላፊነቱን ይረከባል።
2. የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤ ጸሐፊው ይይዛል።
3. ተከሳሹ ተማሪ በጽሑፍና በቃል መልስ የማቅረብ መብት አለው።
4. ከፍተኛና አሳማኝ በሆነ ምክንያት ተማሪው በክርክሩ ሂደት መሳተፍ ያልቻለ እንደሆነ ሲታመን እስከሚችልበት ቀን ድረስ ክርክሩ እንዲቆይ ይደረጋል፤
5. ተከሳሹ ክሱን ለማስረዳት ከሳሽ ያቀረባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ መብት አለው። ከሳሽም ተከሳሽ ያቀረባቸውን የመከላከያ ምስክሮች የመጠየቅ መብት አለው።
6. ተከሳሹ ዝም የማለት መብት አለው። ነገር ግን ዝምታው አምኖ እንደመቀበል ይቆጠራል፤
7. ተከሳሹ አማርኛ የማይችል ከሆነ ሀሳቡን በእንግሊዘኛ የማቅረብ መብት ይኖረዋል።

ክፍል ስምንት
የቅጣት አወሳሰን

አንቀጽ 43፡- ቅጣት ስለማቅለል

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ምክንያቶች ለዲስፕሊን ጥፋቶች ለሚሰጡ ቅጣቶች የቅጣት ማቅለያ ሊሆኑ ይችላሉ።

1. ጥፋተኛው ከዚህ በፊት መልካም ስነ ምግባር የነበረው መሆኑ ከመዝገብ ሲረጋገጥና ከዚህ በኋላ የመድገም ሀሳብ የሌለው እንደሆነ በመፀፀት በጽሑፍ ያቀረበ ከሆነ፤
2. ጥፋቱን የፈፀመው ከባድ አደጋ እየደረሰበት መስሎት ራሱን ለመከላከል በሚያደርገው ሙከራ ከሆነ፤
3. ጥፋቱን እንዲፈፀም የተጐጅው እጅ ካለበት፤
4. ጥፋቱን ሲፈጽም አጥፊው በከፍተኛ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጭንቀት ውስጥ ከነበረ፤
5. ጥፋተኛው የሚጠበቅበትን ሁሉ በማድረግና ጥፋቱን በማመን ከፍተኛ የመፀፀት አዝማሚያ ያንፀባረቀ እንደሆነ፤

አንቀጽ 44፡- ቅጣት ስለማክበድ

የዲስፕን ጥፋት በፈጸሙ ተማሪዎች የሚተላለፍ የቅጣት ውሳኔ ላይ ቅጣቱን ሊያከብዱ የሚችሉ ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. ተደጋጋሚ፣ በሌሊት ወይም ጨለማን ተገን በማድረግ፣ የጦር ወይም ሌላ አደገኛ መሳሪያ በመያዝ ከሆነ፣
2. ጥፋቱን የፈፀመው ከሌሎች የወንጀለኞች ቡድን ጋር በመሆን በተለይ በመሪ ተዋናይነትና አደራጅነት ከሆነ፣
3. ጥፋቱን የፈጸመው በቡድን በመሆን ጥፋቱ የከበደና በሌላው ላይ አስቦና ሆነ ብሎ ጉዳት ለማድረስ ከሆነ፣
4. ጥፋቱን የፈፀመው በማናለብኝነት፣ የተማሪውን አደራ ወደ ጐን በመተው ሆን ብሎ ለማጥፋት አስቦ ከሆነ፣
5. ጥፋቱን የፈፀመው በከፍተኛ ጥላቻ በመነሳት ወይም ሆን ብሎ አስቦበት ከሆነ፣
6. ጥፋቱን የፈፀመው ለጥል ባልተዘጋጁና ባላሰቡ ንጹሀን ተማሪዎች ወይም የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች፣ መምህራን ወይም በአስተዳደር ሠራተኞች ላይ ከሆነ፣

አንቀጽ 45፡- የዲስፕሊን ጥፋቱ በሪከርድነት በተያዘበት ወቅት ሲደገም

1. ቀድሞ ውሳኔ የተሰጠበት የዲሲፕሊን ግድፈት አነስተኛ ግድፈት ሆኖ ውሳኔው የሚያበቃበት ጊዜ ሳይደርስ በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ የሚገኝ የድስፕሊን ጥፋት ከተደገመ እስከ አንድ ወሰነ ትምህርት ከትምህርት ገበታ ያሳግዳል፡፡ የተደገመው ግድፈት አነስተኛ የዲስፕሊን ጥፋት ካልሆነ ግን በአዲስ መልኩ ይታያል፡፡
2. ቀድሞ ውሳኔ የተሰጠበት ጥፋት ቀላል ሆኖ በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ የሚገኝ ጥፋት ወይም አነስተኛ ጥፋት ከተደገመ ከአንድ እስከ ሁለት ዓመት ከትምህርት ገበታ ያሳግዳል፡፡ የተደገመው ጥፋት መካከለኛ ወይም ከፍተኛ ከሆነ ሙሉ በሙሉ ከትምህርት ገበታ ያሰናብታል፡፡
3. ቀድሞ ውሳኔ የተሰጠበት ጥፋት መካከለኛ ወይም ከፍተኛ ከሆነ የትኛውም ጥፋት ቢፈጽም ሙሉ በሙሉ ከትምህርት ገበታ ያሰናብታል፡፡

አንቀጽ 46፡- ተደራራቢ የዲሲፕሊን ጥፋት ሲፈፀም የቅጣት አወሳሰን

ተማሪው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከትምህርት ገበታ የሚያሳግዱ የዲሲፕሊን ግድፈቶች በአንድ ጊዜ ወይም በመጀመሪያ ለፈፀመው ጥፋት ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት ፈጽሞ ከተገኘ ለእያንዳንዱ ጥፋት ቅጣት ከተቀመጠ በኋላ የሁሉንም ቅጣት በመደመር ይወሰናል፡፡ የሁሉም ድምር ከሶስት ዓመት ከበለጠ ሙሉ በሙሉ ከትምህርት የማሰናበት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

አንቀጽ 47፡-ውሳኔን ስለማሳወቅና ተያያዥ ጉዳዮች አፈጻጸም

1. ከምክር (ከግሳፄ) በስተቀር ማንኛውም በተማሪ ላይ በዲስፕሊን ጥፋት የሚወሰድ እርምጃ ለተማሪው በጽሑፍ ሊሰጠው ይገባል፡፡
2. በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በማንኛውም ደረጃ የሚወሰድ የዲስፕሊን ጥፋት እርምጃ ቢያንስ ለግቢ ደህንነትና ጥበቃ፣ ለሚመለከተው የትምህርት ክፍል ኃላፊ፣ ለሚመለከተው ኮሌጅ/ፋኩልቲ ዲን፣ ለሪጅስትራር፣ ለተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር፣ ለአስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንትና ለፕሬዚዳንት በግልባጭ ማሳወቅ ይገባል፡፡ የተጠቀሱት አካላትም በአግባቡ አደራጅቶ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡

3. ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በሙሉ በግልጽ በሚታይ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ሌላው እንዲማርበት ይደረጋል።
4. ተማሪው ባጠፋው ጥፋት በጊዜያዊነትም ይሁን ሙሉ በሙሉ ከትምህርት ገበታ በሚታገድበት ወቅት የታገደበት ምክንያት በጽሑፍ ይገለጽለታል። በወቅቱ ተማሪው በግቢ ውስጥ ባለመገኘቱ ወይም አድራሻው ባለመታወቁ ወይም በሌላ ምክንያት በአካል ሳይገኝ በመቅረቱ ከትምህርት ገበታ የታገደበትን ውሳኔ ለራሱ መስጠት ካልተቻለ ውሳኔው በዩኒቨርሲቲው ማስታወቂያ ሰሌዳ ቢያንስ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ተለጥፎ እንዲቆይ ይደረጋል።
5. ተማሪው የተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ከትምህርት ገበታው እንዲታገድና የትምህርት ማስረጃው እንዳይሰጠው ካልተወሰነበት በስተቀር እስከ ዕግዱ ያለው የትምህርት ማስረጃ በዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ያቋረጠ መሆኑን ከሚገልጽ ሽኚ ደብዳቤ ጋር ይሰጠዋል።
6. የተማሪው በጊዜያዊነትም ይሁን ሙሉ በሙሉ ከትምህርት ገበታው መታገድ ከዕግዱ ጋር ያልተያያዙ መብቶችንና ግዴታዎቹን ተፈጻሚነት አያስቀርም።
7. ውሳኔ ለመስጠትም ይሁን ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር እና የተማሪዎች ህብረት የውሣኔ መጓተት እንዳይፈጠር አፈፃፀሙን ይከታተላሉ።

አንቀጽ 48፡- የዲስፕሊን ጥፋት ቅጣትን በሪከርድነት ስለመያዝ

ማንኛውም ተማሪ የዲሲፕሊን ጥፋት የቅጣት ውሳኔ ከተላለፈበት በኋላ በግል ፋይሉ ውስጥ ገብቶ በሪከርድነት ሊያዝበት የሚችለው

1. ለአነስተኛና ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች ቅጣት ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ብቻ የሚቆይ ሲሆን በተማሪው ማህደር ውስጥ ከአንድ ዓመት በላይ ተቀምጦ ቢገኝ ዋጋ አይኖረውም።
2. ለመካከለኛ፣ ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች ውሳኔ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ተማሪው ትምህርቱን እስካጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ሆኖ በሰነድነት ግን በተመራቂው ፋይል ውስጥ ሁሌም ይቀመጣል።

አንቀጽ 49፡- የዲስፕሊን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት

1. ማንኛውም ተማሪ አነስተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶችን በሚፈጽምበት ወቅት ጉዳዩን ለዲስፕሊን ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ፡-
   ሀ. የዲስፕሊን ጥፋቱ በተፈጸመበት ክፍል ኃላፊ (ወይም ጥፋቱ በመማሪያ ክፍል፣ በወርክሾፖችና በቤተ ሙከራ ክፍሎች ከሆነ በመምህሩ፣ ከዚያ ውጭ ከሆነ የትምህርት ወይም የሥራ ክፍል ኃላፊ) ምክር ወይም የቃል ማስጠንቀቂያ የመስጠት እና ይህንኑ በመዝገብ መዝግቦ የመያዝ ኃላፊነት አላቸው።
   ለ. የትምህርት ክፍል ኃላፊ፣ ኮሌጅ/ፋኩልቲ/ኢንስቲትዩት ዲንና የተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ሥልጣንና ኃላፊነት አላቸው።
2. ማንኛውም ተማሪ ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች የፈጸመ እንደሆነ ኮሌጅ/ፋኩልቲ/ኢንስቲትዩት ዲን በዚህ መመሪያ መሠረት በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ ሲቀርብለት በፋይል የሚቀመጥና በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ የሚለጠፍ ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ወይም/እና ማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣንና ኃላፊነት አለው።
3. ማንኛውም ተማሪ መካከለኛ፣ ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋቶች የፈጸመ እንደሆነ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት በዚህ መመሪያ መሠረት

በዲስፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ ሲቀርብለት እንደጥፋቱ ክብደት በፋይል የሚቀመጥና በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ የሚለጠፍ ከከባድ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ጀምሮ ከትምህርት ገበታ እስከማገድ ወይም ሙሉ በሙሉ እስከማሰናበት ሥልጣንና ኃላፊነት አለው።

ክፍል ዘጠኝ

ልዩ የክርክር ሂደት

አንቀጽ 50፡- ጉዳዩ በሴኔት ስለመታየት

ለሁለትና ከዚያ በላይ ዓመት ከትምህርት ገበታ ሊያስናብቱ የሚችሉ የዲስፕሊን ጥፋቶች ላይ በወቅቱ በተከሰተው ችግር አሳሳቢነት የተነሳ ሴኔቱ ማየት ሲፈልግ ጉዳዩን የመመርመር፣ የማጣራትና ቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ በማጽደቅ፣ በማሻሻል ወይም በመሻር ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አለው። ይህም የሚሆነው ጉዳዩ በሴኔት እንዲታይ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሲወሰን ነው።

ክፍል አስር

የይግባኝ ስነ-ሥርዓት

የይግበኝ ውሳኔ አሠጣጥ ሂደቱ ከዲስፕሊን ጥፋት ክስ አመሠራረት እስከ ውሳኔ አፈጻጸም ድረስ ካለው ጋር ተመሳሳይ ሂደትን የሚከተል ነው።

አንቀጽ 51፡- የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም

የዩኒቨርሲቲው ኘሬዚዳንት የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ያቋቁማል።

የኮሚቴው አባላት፡-

1. አንድ የሰኔት አባል የሆነ መምህር.....ሰብሳቢ
2. አንድ የአስተዳደር ክፍል ሃላፊ .....ፀሐፊ
3. አንድ የተማሪዎች ህብረት አባል.....አባል

አንቀጽ 52፡- ይግባኝ የማቅረብ መብት

ሀ. ጥፋተኝነት የተወሰነበት ተማሪ ቅሬታውን (ይግባኙን) ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ እንዲቀርብለት ለዩኒቨርሲቲው ኘሬዚዳንት ውሳኔው ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማመልከቻ የማቅረብ መብት አለው። የይግባኝ ማመልከቻውም የሚከተሉትን መያዝ አለበት።

1. የይግባኝ አቅራቢ ስም፣ መለያ ቁጥር፣ ጾታና እድሜ
2. የሚማርበት ፋካሊቲ፣ ትምህርት ክፍልና የትምህርት ዓመት
3. የቅሬታው መንስኤ
4. ደጋፊ ማስረጃዎች /ካሉ/
5. አመልካች የሚሻው መፍትሄ
6. ቀንና ፊርማ

ለ. የዩኒቨርሲቲው ኘሬዚዳንት በወቅቱ የቀረበውን ቅሬታ አይ ፕሬዚዳንቱ መጣራ አለበት ብሎ ስያምን የተጻፈውን ማመልከቻ ከአስፈላጊ መረጃ ጋር ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ልመራው ይችላል።

ሐ. ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በፕሬዚዳንቱ የተመራለትን ማስረጃዎች አግባብነት ካላቸው የዩኒቨርሲቲው ህጎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች አንፃር በመመርመር በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ቅጣቱን ሊያፀድቀው፣ ሊያሻሽለው ወይም ውድቅ እንዲሆን ወይም እንደገና

በዲስፒሊን ኮሚቴ እንዲመረመር ወይም ለየት ያለ ቅጣት እንዲወሰን ከዚህ መመሪያ ጋር የተገናዘበ አማራጭ የውሳኔ ሃሳብ ለፕሬዚደንቱ ሊያቀርብ ይችላል። በዚህ ላይ ፕሬዚዳንቱ ውሳኔ ይሰጣል።

መ. ይግባኝ የሚቀርብባቸው ጉዳዮች መካከለኛና ከዚያ በላይ ምድብ ላይ ለሚገኙ የዲስፕሊን ጥፋቶች ላይ በተላለፈ ውሳኔ ላይ ነው።

አንቀጽ 53፡ የይግባኝ መሠረቶች

1. በዲስፕሊን ኮሚቴ ታይቶ በአስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት በጸደቀ የዲስፕሊን እርምጃ ላይ ቅሬታ ሲኖር
2. አዲስ ማስረጃ ካልተገኘ በስተቀር ይግባኝ መሠረት የሚያደርገው የተማሪዎች የዲስፕሊን ኮሚቴ ባሰባሰባቸው ማስረጃዎችና በውሳኔ መዝገብ ላይ ብቻ ነው። አዲስ የክስ ጭብጥ በይግባጭ ላይ አይቀርብም።
3. የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኙን ማየት አግባብ ሆኖ ካገኘው፡
   ሀ. የመጀመሪያ ክርክሩ ስነ-ስርዓቱን ጠብቆ ስለመካሄዱ፣
   ለ. የተወሰነው ውሳኔ በቂ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ
   ሐ. ቅጣቱ ተማሪው አጥፍቷል ለተባለው ጥፋት ተመጣጣኝ ስለመሆኑ
   መ.ተከሳሹ በዋናው ክርክር ሂደት ወቅት ሊያገኘው ያልቻለውና ውሳኔ ማስቀየር የሚችል ማስረጃ ካቀረበ ኮሚቴው የቀረበውን ማስረጃ መርምሮ በአንድ ሳምንት ውስጥ የውሳኔ ሐሳቡን ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር በማያያዝ ለኘሬዚዳንቱ በጽሑፍ ያቀርባል።

አንቀጽ 54፡- የቅጣት አፈፃፀም

1. በተማሪው ላይ የተወሰነውን ውሳኔ በማስታወቂያ ከወጣበት ሰዓት ጀምሮ ውሳኔው በጥፋተኛው ላይ ተግባራዊ ይሆናል፣
2. ተማሪው የይግባኝ ማመልከቻ አቅርቦ ይግባኙ አግባብ መሆኑ ከታመነበትና ተማሪው ሂደቱን ግቢ ሆኖ መከታተል ከፈለገ ግቢ ውስጥ በመቆየቱ በራሱ፣ በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና ንብረት ላይ የሚያመጣው አደጋ አለመኖሩ ከታመነበት የይግባኝ ስርዓቱን እስኪጨርስ ግቢ ውስጥ እንዲቆይ በፕሬዚዳንቱ ሊፈቀድለት ይችላል።

አንቀጽ 55፡- የዩኒቨርሲቲው ኘሬዚዳንት ስልጣንና ኃላፊነት

ሀ. በዲሲኘሊን ጥፋት የተከሰሰ ተማሪ ጉዳይ በውሳኔ ሂደት ላይ እያለ የተከሳሹ ተማሪ ከተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋት ክብደት አንፃር በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ መኖር ለእርሱና ለሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት መልካም አለመሆኑን በማንኛውም መንገድ ፕሬዚዳንቱ ሲያውቅ ጉድዩ ተጣርቶ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ ተጠርጣሪው ሰብዓዊ መብቱ በአግባቡ ተጠብቆለት፣ የምግብና የህክምና አገልግሎት ከዩኒቨርሲቲው ማግኘት በሚችልበት መንገድ በአካባቢው ፖሊስ ቁጥጥር ስር የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል።

ለ. በዚህ መመሪያ መሠረት ከትምህርት ገበታ ሙሉ በሙሉ ለተሰናበቱ ተማሪዎች ኘሬዚዳንቱ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ አስግብቶ ይቅርታ የማድረግ ወይም ውሳኔውን የማሻሻል ሥልጣን አለው። ሆኖም ተማሪው ያጠፋው ንብረት ዋጋ ያለው ከሆነ ተተምኖ ተማሪው እንዲከፍል ማድረጉን አያስቀርም።

ሐ. የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በዲስፕሊን ጥፋት ተከሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ይቅርታ የሚያደርግለት ወይም ውሳኔውን የመገደብ ስልጣኑን የሚጠቀመው

ተማሪው የቀድሞ ሪከርዱንና ከጥፋቱ ተምሮ የተፀፀተ መሆኑን ሲያረጋግጥና ይህንንም የሚገልጽ የይቅርታ ደብዳቤ በጽሑፍ ተማሪው ሲያቀርብና ሲታመንበት ነው።

አንቀጽ 56፡ የመጨረሻ ውሳኔ

በተማሪዎች የዲስፕሊን ጉዳይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ውሳኔ የመጨረሻ ቢሆንም እንደአስፈላጊነቱ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

ክፍል አስራ አንድ
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 57፡- ተባባሪ ስለመሆን

በዚህ መመሪያና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጐች የተከለከሉ ድርጊቶችን ከሚፈጽም ማንኛውም አካል ጋር ተባባሪ የሆነ እና ድጋፍ ሲሰጥ የተገኘ ተማሪ ራሱ የዲሲፕሊን ግድፈቱን እንደፈፀመ ተደርጐ ከዋናው ድርጊት ፈፃሚ ጋር እኩል ይቀጣል።

አንቀጽ 58፡- የዩኒቨርሲቲውን ግቢ ስለመልቀቅ

በውጤት ማነስ ወይም የማቋረጥ ፍቃድ በመጠየቅ ወይም በፈፀመው ዲሲፕሊን ጥፋት መሠረት የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት ተማሪ የሚጠበቅበትን ሂደት በጨረሰበት በ24 ሰዓት ውስጥ ግቢውን ለቆ መውጣት አለበት። ነገር ግን ተማሪው በታቀደለት ጊዜ ሳይወጣ ቢገኝ ሌላ ከፍተኛ የዲስፕሊን ጥፋት በድጋሚ እንደሰራ ተቆጥሮ እንደገና በዲሲፕሊን ይታያል።

አንቀጽ 59፡- የተጠያቂነት ገደብ

ተማሪዎች መብታቸውን ለማስከበር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሂደት በማንም ወይም በምንም ላይ ጉዳት እስካላደርሱ ድረስ ወይም በቅን ልቦና በሚያከናውኑት ተግባር ወይም በአጋጣሚ አደጋ በሚከሰት ነገር ወይም በልዩ ሁኔታ በተፈቀደ ተግባር ላይጠየቁ ይችላሉ።

አንቀጽ 60፡- ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

ከዚህ በፊት ሲሰራበት የነበረው የዩኒቨርሲቲዎች የተማሪዎች የዲሲፕሊን መመሪያ በዚህ መመሪያ የተተካ በመሆኑ ተፈፃሚነት አይኖረውም። የተማሪዎች ዲስፕሊንን የሚመለከቱ ሌሎች ህጎችና ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

አንቀጽ 61፡- መመሪያውን ስለማሳወቅ

1. የእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት አዲስ ተማሪዎች ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት እና ለነባር ተማሪዎችም እንደአስፈላጊነቱ ይህንን መመሪያ በዝርዝር የማሳወቅ ግዴታ አለበት።
2. ዩኒቨርሲቲው ይህ መመሪያ ለተማሪዎችና ሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት በተለያየ መንገድ ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል።

አንቀጽ 62፡-የመተባበር ግዴታ

ለዚህ መመሪያ ተግባራዊነት ሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበረሰብ አባላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

አንቀጽ 63፡- መመሪያውን ስለማሻሻል
ይህ መመሪያ አጥጋቢ ምክንያቶች ሲኖሩ ወይም በዩኒቨርሲቲዎች ጥያቄ ሲቀርብ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር አማካይነት ሊሻሻል ይችላል።

አንቀጽ 64፡- መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ
ይህ መመሪያ ከመስከረም 01 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሂሩት ወልደማሪያም (ፕሮፌሰር)
ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሚንስትር
መስከረም 2012 ዓ.ም - አዲስ አበባ